«ሰማዕታት የዚህችን ዓለም ጣዕም በዕውነት ናቁ
ደማቸውንም ስለ እግዚአብሔር አፈሰሱ፡፡
ስለ መንግሥተ ሰማያትም መራራ ሞትን ታገሱ፡፡»
የሐሙስ ውዳሴ ማርያም

# ስምዐ ጽድቅ



## ማውጫ


፪ አጫጭር ዜናዎች
፬ መልእክት
፮ ሪፖርታዥ
፱ ቤተ አብርሃም
፲፪ ቃለ መጠይቅ
፲፭ የሕፃናት ዓምድ
፲፯ ትዝብት
፲፰ ምሥጢሬን ላካፍላችሁ



ስምዐ ጽድቅ

የቤተ ክርስቲያኒቱን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ማኅበረ ቅዱሳን በኅትመት ሚዲያ መምሪያ እየተዘጋጀ በወር ሁለት ጊዜ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ

ጳጉሜን ፭ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም. ተጀመረ



☎ 011-1553555/ 011-1553442
✉ 80078
<u>አዲስ አበባ</u>

የዝግጅት ክፍሉ ኢሜይል
newspaper@eotcmk.org



ምክትል ዋና አዘጋጅ
ወርቅነሽ ቱፋ
ከፍተኛ ሪፖርተር
ካሣሁን ለምለሙ
ሪፖርተር
ምኒልክ ብርሃኑ
የገጽ መልክ (Layout) ዲዛይነርና
ጸሐፊ
ገነት ታደሰ



በጣና ሐይቅ የሚገኙ አድባራት፣ ገዳማትና የተፈጥሮ ሀብት በከፊል

# የጣና ሐይቅ ገዳማት፣ አድባራትና የተፈጥሮ ሀብቶች በዩኔስኮ በማይንቀሳቀሱ ቅርሶች ዘርፍ ለማስመዝገብ እየተሠራ መሆኑ ተገለጸ

*ካሳሁን ለምለሙ*

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በባሕር ዳር ሀገረ ስብከት የሚገኙት የጣና ሐይቅ ገዳማት፣ አድባራትና የተፈጥሮ ሀብቶች በዩኔስኮ በማይዳሰሱ ቅርሶች ዘርፍ በቋሚነት ለማስመዝገብ እየተሠራ መሆኑን የአማራ ክልል ቱሪዝም ቢሮ ማስታወቁን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቴሌቪዥን ጣቢያ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ ቲቪ) ዘገበ፡፡

ከዘገባው መረዳት እንደተቻለው የጣና ሐይቅ ገዳማት፣ አድባራት፣ የተፈጥሮና የባህል ቅርስ በመንግሥታቱ ድርጅት የባህል፣ የሳይንስና የትምህርት ተቋም (ዩኔስኮ) በኩል በጊዜያዊነት በዓለም ቅርስ መዝገብ ሠፍረዋል፡፡

የአማራ ክልል ቱሪዝም ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ኤርሚያስ መኮንን ለአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን (አሚኮ) ያስተላለፉትን መልእክት ዋቢ አድርጎ ዘገባው እንዳስረዳው ቱሪዝም ቢሮው ከፌዴራል ቅርስ ጥበቃ ባለሥልጣን ጋር በመተባበር ጣና ሐይቅና በውስጡ ያሉ ገዳማት፣ አድባራት፣ የተፈጥሮና የባህል ቅርሶችን በዩኔስኮ ለማስመዝገብ ሲሠራ መቆየቱን ገልጧል፡፡

አቶ ኤርምያስ አያይዘውም "በጣና ሐይቅና አካባቢው ያሉ ሥፍራዎች የሃይማኖትና የፍልስፍና ትምህርቶች ሲሰጥባቸው የኖሩና የዓለም ምስጢራት ይገኝባቸዋል ተብሎ የሚታሰቡ መሆናቸው ዩኔስኮ በጊዜያዊነት በማይንቀሳቀሱ ቅርሶች ዘርፍ እንዲመዘግባቸው የራሱ የሆነ ድርሻ ነበረው" ብለዋል፡፡ "ቅርሶች በዓለም አቀፍ ተቋም መመዝገባቸው ጥበቃ እንዲደረግላቸው፣በዓለም ዙሪያ እንዲተዋወቁና የምጣኔ ሃብት ምንጭ ሆነው እንዲቀጥሉ የማድረግ አቅም ይፈጥርላቸዋል" ሲሉም አክለዋል፡፡

አካባቢው በጊዜዊነት በዩኔስኮ በቅርስነት መመዝገቡ በጣና ሐይቅና ዙሪያው ያሉ ብዝኃ ሕይወትን ጠብቆ ለትውልድ ለማሸጋገር እንደሚያስችል የገለጡት ምክትል ኃላፊው ቅርሶቹን በቋሚነት ለማስመዝገብም እየተሠራ መኾኑንም አብራርተዋል፡፡

በጣና ሐይቅ ዞሪያ የሚገኙ ገዳማት፣ አድባራትና የተፈጥሮ ሀብቶች በዓለም ቅርስነት በቋሚነት ሲመዘገብ ሃይማኖታዊ ሥርዐቱን በጠበቀና ኢትዮጵያዊ ዕሴትን ባከበረ ምልኩ እንደሚሆን ኃላፊው ገልጠው በአሁኑ ሰዓት ቅርሶቹን በቋሚነት የማስመዝገቡ ሂደት በጥሩ ሁኔታ ላይ መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

በመጨረሻም ቅርሶቹን በቋሚነት ለማስመዝገብ የሚደረገው ጥረት ላይ የግልና የመንግሥት ተቋማት፣ ታዋቂ ግለሰቦችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ድጋፍ እንዲያደርጉ ኃላፊው ጥሪ አቅርበዋል፡፡



በመሠራት ላይ የነበረው የደብረ ዕንቍ ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያ ን የመስቀል ፕሮጀክት

# ፍርድ ቤቱ ደብረ ዕንቍ ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን ላቀረበችው አቤቱታ ብይን ሰጠ

ካሳሁን ለምለሙ

በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት በየካ ወረዳ ቤተ ክህነት ሥር በምትገኘው ደብረ ዕንቍ ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን ሕጋዊ ይዞታ ላይ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለሥልጣን እየፈጸመባት ያለውን ሕገ ወጥ ድርጊት እንዲያቆም ባቀረበችው አቤቱታ መሠረት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ ፲፯ኛ ፍትብሔር ችሎት ሰኔ ፳፬ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም በዋለው ችሎት ብይን መስጠቱ ተገለጠ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለሥልጣን ከጥር ወር አጋማሽ ፳፻፲፬ ዓ.ም ጀምሮ በደብረ ዕንቁ ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን ሕጋዊ ይዞታ ላይ የተለያዩ የቁፋሮ ሥራ የሚያከናውኑ ማሽነሪዎችን በማስገባት የግንባታ መሠረቶችን በመጣልና በቤተ ክርቲያን ይዞታ ላይ ሁከትና ብጥብጥ መፍጠሩ በክሱ አቤቱታ ተመላክቷል፡፡

ቤተ ክርስቲያን በይዞታዋ ላይ የተፈጠረውን ችግር በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ጥረት ስታደርግ ቆይታ ባለመሳካቱ ክስ መመሥረቷን በአቤቱታው የተገለጠ ሲሆን በአንጻሩ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለሥልጣን ከተንኳሽነቱና ከግንባታ እንቅስቃሴው እንዳልታቀበ ተመላክቷል፡፡

ቤተ ክርስቲያን ለፍርድ ቤቱ የሰውና የሰነድ ማስረጃ አቅርባ ለተወሰኑ ወራቶች ስትከራከር ቆይታ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ ፲፯ኛ ፍትብሔር ችሎት ሰኔ ፳፬ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም በዋለው ችሎት ብይን መስጠቱ የታወቀ ሲሆን ተከሳሹ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለሥልጣን በቤተ ክርቲያን ሕጋዊ ይዞታ ላይ የግንባታ እንቅስቃሴ ሲያካሄድ እንደነበር እንዲሁም ሁከትና ብጥብጥ ሲፈጥር መቆየቱን ፍርድ ቤቱ በምርመራው አረጋግጧል፡፡

በዚህ መሠረት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የልደታ ምድብ ፲፯ኛ ፍትብሔር ችሎት በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት በየካ ወረዳ ቤተ ክህነት በምትገኘው ደብረ ዕንቍ ልደታ ለማርያም ቤተ ክርስቲያን 103,952 ካሬ ሜትር ሕጋዊ ይዞታ ላይ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መንገዶች ባለሥልጣን የሚያካሄደውን የግንባታ ሥራ፣ የሁከትና የብጥብጥ ተግባር እንዲያቆም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

# ቤተ ክርስቲያንን ለማሻገር የሙሴን መንገድ እንከተል!

ቤተ ክርስቲያን ከምንግዜውም በላይ በብዙ ፈተና ውስጥ እያለፈች ትገኛለች፡፡ ከቀን ወደ ቀን እየተባባሰ የመጣው፤ በሁሉም አቅጣጫ መንፈሳዊ አገልግሎቷን ለማዳከም እየተካሄደባት ያለው እኩይ ሤራ፤ እየደረሰባት ያለው መከራ ከሁሉም የቤተ ክርስቲያን ልጅ የተሰወረ አይደለም፡፡ ስለ ሀገር፣ ስለ ዓለም ሰላም አብዝታ የምትጸልየው፣ በዐውደ ምሕረቷ የምትሰብከው ቤተ ክርስቲያን ሰላሟን እያጣች ነው፡፡ ምእመናን በየቦታው እየታረዱ፣ አብያተ ክርስቲያናት እየተዘረፉ እየተቃጠሉ አገልጋይ ካህናትዋ እየተሰደዱ፣ ሉዓላዊነቷን፣ ክብሯን እንድትነፈግ እየተደረገች ነው፡፡ በአጠቃላይ ከአምላክ የተሰጣትን ሰማያዊውን አገልግሎት እንዳትፈጽም እንቅፋቷ በአንድም በሌላም ምክንያት እየበዛ ነው፡፡

ትላንት ራሷን ከምታስተዳድርበት፣ አገልጋይ ካህናቷን ከምትደጉምበት እንዲሁም ከራሷ አልፋ ሌሎችን ከምትረዳበት ሀብትና ንብረቷ እንድትገፋ ስትደረግ ኖራለች፡፡ ሀልዎተ እግዚአብሔርን እንድትዘነጋና የኮሚኒዝም እምነት እንድትከተል በእርሷና በእምናንዋ ላይ የተካሄደው ኢ-ኦርቶዶክሳዊ ዘመቻ ቀላል አይደለም፡፡ ከሉዓላዊነትዋ ለማውረድ የተከፈተባትን ዘርፈ ብዙ ተግዳሮት ተቋቁማ ዛሬ ላይ ብትደርስም ጥሎባት ያለፈው ጠባሳ ምልክቱ ዛሬም ጎልቶ የሚታይ ነው፡፡

አንገትዋን ቀና አድርጋ እንዳትሄድ፣ በድፍረት እንዳትናገር የትናንት ተሰሚነቷን፣ መከበሯን እንድታጣ በየጊዜው ሲደርስባት የነበረው ጫና ከውስጥም ከውጪም በተነሡባት አጽራረ ቤተ ክርስቲያን መሆኑ የዐደባባይ ምሥጢር ነው፡፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከአብራኳ በወጡ ልጆች እጅግ ተፈትናለች፡፡ እምነትዋን፣ ዶግማዋን ፣ ቀኖናዋንና ሥርዓቷን ለማጥፋት በሄዱት ርቀት ልክ ዋጋን ከፍላለች፡፡ መናፍቃን፣ ግዙፍነቷ፣ ተፈሪነቷ፣ ሀገርነቷ ባስፈራቸው ባለጊዜዎች በተለያየ መንገድ ስትገፋ ኖራለች፡፡

እንደቅርጫ ተካፍለው መከራዋን ባበዙባት መጠን ተንገዳግዳ ለመቆም ብትሞክርም የማያቋርጠው ዘርፈ ብዙው ግፊያ ከዚህም ወደ ከፋ እልቂት እንዳይጥላት ያሰጋል፡፡ እውነተኛዋና ቀጥተኛዋ እምነት፣ የብዙዎች እናት እና ቀደምት መሆንዋ የሚያስፈራቸው፤የሀገር ባለውለታና የታሪክ ምንጭ ሆና መገኘቷ የሚያስጋቸው ከግለሰብ እስከ ቡድን ብዙዎች ናቸው፡፡ ግዘፍ ነስታ መታየቷ ትንሽነታቸውን የሚያሳብቅባቸው የሚመስላቸው፤ እንደ ፈርኦን ሙሴዎቿን ለመግደል የሚሯሯጡ፤ መንጋዎቿን ለመበተን የሚያሤሩ ብዙዎች እንደሆኑ የታወቀና የተረዳ ነገር ቢሆንም ራስን ለመከላከልና ቤተ ክርስቲያንን ለመታደግ የተዘጋጀና የተሟላ ስነ ልቡና፤ ብቃት ያለው ቁመና ላይ ነን ወይ? የሚለው ግን አጠያያቂ ነው፡፡

ለዚህ ደግሞ በሌላው ላይ ጣት መጠቆም መፍትሔ አይሆንም፡፡ ለቤተ ክርስቲያን እነ እገሌ አሉ ብሎ ተዝናንቶ መቀመጥ ያሉባትን ችግሮች ከሥሩ አይነቅልም፡፡ ከታናናቹ እስከ ታላላቆቹ ሌሎችን መተቸት የቤተ ክርስቲያንን የዘመናት ቍስል ከማባባስ ውጪ አንዳች ቀዳዳ አይደፍንም፡፡ አንዱ ሌላውን በመንቀፍ፣ በመለያዬትና ለየብቻ በመሮጥ ውጤት አይመጣም፡፡ ይልቁንም እያንዳንዱ ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን የሚጠበቅበትን ድርሻ ጠንቅቆ ሲያውቅና ለዚያም በርትቶ ሲሠራ መሠረቱ ጸንቶ ሊቆም ይችላል፡፡ አንዱ ሌላውን ሲሰማው፤ አንዱ ሌላውን ሲያከብረው፤ አንዱ ሌላውን ከእኔ የተሻለ ነው ብሎ ሲያስብ ያኔ ለቤተ ክርስቲያን ችግር መፍትሔ ይገኛል፡፡ በዚያ ልክ አርቆ ማሰብ ከሁላችንም ይጠበቃል፡፡

ቤተ ክርስቲያን የልጆቿን የልብ ትርታ በትክክል ልትሰማ፤ በሁለት ወገን የተሳሉ፣ ክርስቲያኖች እንዲሆኑ በማብቃት ደረጃ ዘመኑን በዋጀ መልኩ ልትከውን ይገባል፡፡ የትናንት የቤተ ሥራዎቿን አይታ ተገቢ መልስ መስጠት ዛሬ እየደረሰባት ያለውን ችግር በእጅጉ እንደሚቀንስ መረዳት ከባድ አይደለም፡፡ ቤተ

ክርስቲያን የሁሉ ነገር መሠረት ነትና ከእርስዋ ብዙ ቢጠበቅም የብቻዋ ሥራ ነው ብሎ ማሰብም ከየዋህነት ያለፈ ዘመኑንም አለመዋጀት ጭምር ነው። ቤተ ክርስቲያን ዛሬ ላይ እያሳለፈች ያለውን ፈተና እኔ ላይ አልደረሰም ብሎ ማሰብ የዋህነት ብቻ ሳይሆን ከቤተ ክርስቲያን ኅብረት የሚያወጣ ነውና ነገን ማየት ከሁላችንም ይጠበቃል።

ቤተ ክርስቲያን ያስተማረችንን፤ ዛሬም በዐውደ ምሕረቷ እያስተማረች ያለችውን በሕይወት መኖር ባለመቻላችን፣ አንድ ላይ ጉባኤ ብንካፈልም፣ ብናስቀድስም፣ ብንዘምርም፣ ለበዓላት ብንሰበሰብም አንድ አይደለንም። በቤተ ክርስቲያን ጉዳይ አንድ መሆን ቢገባንም ሐሳባችን እንደመልካችን የተዝጎረጎረ ነው። ሰምቶ ሂያጆች ብቻ መሆናችን፣ ብዙዎቻችን ለጊዜያዊ ስሜት ቅርብ መሆናችን ለቤተ ክርስቲያን ችግር ለአንድ ሰሞን ብቻ እንድንሆን አድርጎናል። ሐዋርያው እንዳለው ነገሮችን በሚገባ እንዳናስተውል አዚም ያደረገብን ማን ይሆን? እንግዲያው ከተኛንበት ልንነቃ ይገባል። ቤተ ክርስቲያን ዛሬ ላይ እያለፈችበት ያለውን ፈተና ሁላችንም በውል ልንረዳ የራሳችን ሕመም መሆኑን ማወቅ ቀዳሚው ተግባር ነው። በፈረሰው በኩል ለመቆም የሚያስተውል አእምሮ ፣ እንደ አንድ ልብ የሚያስብ ኦርቶዶክሳዊ ኅብረት ያስፈልገናል።

የቤተ ክርስቲያን ጉዞ ሁሌም የመስቀል ጉዞ እንደሆነ ቢታወቅም መስቀሉን በኅብረት መሸከም ክርስቲያናዊ ባሕል መሆኑን መዘንጋት አያስፈልግም። ‹‹ ሰማዕትነት አያምልጠን›› እያሉ ከአራቱም ማዕዘን ተጠራርተው በደማቸው ያቆዩልን የሰማዕታት ቤት ናትና የተቀበልነውን በክብር ጠብቆ ለትውልድ ለማስረከብ ለእኛ ለኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ከዛሬ ሌላ መልካም ዕድል የለም። እውነተኛ ክርስቲያን ሆነው በየዘመኑ የሚመጣውን ፈተና ተቋቁመው ያስረከቡንን ቤተ ክርስቲያን በስም ክርስቲያን ተጠልለን፣ በማስመሰል ካባ ተሸፍነን መኖሩ ከክርስቲያን ተርታ የሚያቆመን አይደለም። ልጆችዋ ነን ለምንላት ቤተ ክርስቲያንም አንዳች አይረባምና በየዕለቱ ከቤተ በክርስቲያን ደስታና መከራ ጎን መቆም ይጠበቅብናል።

ቤተ ክርስቲያን እያሳለፈች ያለው ዘርፈ ብዙ ተግዳሮት ዐዲስ ባይሆንም ዛሬ ላይ ያለነው ትውልድ ግን የአባቶቻችንን ፈለግ ተከትለን ቤተ ክርስቲያንን መታደግ አልቻልንም። በእኛ ዕድሜ እያየነው ያለፍነው የቤተ ክርስቲያን ሰቆቃ ያለና የነበረ፤ ሆኖም በብርቱ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ድል ተነሥቶ ቤተ ክርስቲያንን በክብር ያቆመ እኛ ጋር እንድትደርስ ማድረጉን መዘንጋት ተገቢ አይደለም። ትላንትን በውል ተረድቶ፤ ነገን በጥንቃቄ አስልቶ መሄድ ከአባቶቻችን የወረስነው ጥበብ ነውና ለዚህ ልንተጋ ይገባል። ዘመነ ሰማዕታትን ተሻግራ ከኛ የደረሰችውን ቤተ ክርስቲያን ለማሻገር እኛም የሙሴን ፈለግ መከተል፣ በዚያ ልክ መሮጥም ይገባናል መልእክታችን ነው።

# ከመንፈሳዊ ተቋማት የሚወጡ ደቀ መዛሙርት እና የአብነት መምህራን ለገጠሪቱ ቤተ ክርስቲያን

እንዳለ ደምስስ

በተለያዩ ዘመናት ለቤተ ክርስቲያን ዋስ ጠበቃ የሆኑ አባቶች ከተለያዩ መንፈሳዊ ትምህርት ቤቶች ተምረው በዓለም ዙሪያ ለአገልግሎት በመሰማራት ክርስትናን ሰብከዋል፡፡ ይደርስባቸው የነበረውን መከራም ታግሠው ከአንዱ ሀገር ሲሰደዱ ወደ ሌላው በመንዝ ዓለምን በወንጌል ጨውነት አጣፍጠዋል፡፡ ታዲያ እነዚህ አባቶች ቃለ እግዚአብሔርን በቃል ብቻ ከማዳረስ አልፈው ዛሬ እኛ ትውልድ ድረስ መሻገር የቻሉ ወደፊትም የሚሻገሩ ዘመን የማይገታቸው መጻሕፍትንም ፊደል ቀርጸው፣ ብራና ዳምጠው፣ ቀለም በጥብጠው በጽሑፍ ማዘጋጀት ችለዋል፡፡ በትሕትና እና በፍጹም ታዛዥነት የእግዚአብሔርን ስም መሪ አድርገው ተጉዘዋልና ቁጥር ስፍር የሌላቸው ደቀ መዛሙርትንም ለማፍራት በቅተዋል፡፡ ለዚህ መነሻ የሆናቸው ግን በዓለም ላይ አሉ ከሚባሉ መንፈሳውያን ትምህርት ቤቶች ከአባቶቻቸው እግር ሥር ቁጭ ብለው በትዕግሥት በመማራቸውና ለአገልግሎት ከእግዚአብሔር በተሰጣቸው ጸጋ ለማገልገል በመዘጋጀታቸው ነው፡፡

ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዋለበት እየዋሉ ባደረበት እያደሩ የቃሉን ትምህርት እየተመገቡ፣ የእጁን ተአምራት እያዩ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ሲማሩ የቆዩ ሐዋርያትን አደራም ተቀብለዋል፡፡ "እንግዲህ ሂዱና በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ፡፡ ያዘዝኋችሁንም እንዲጠብቁ አስተምሯቸው፤ እኔም እስከ ዓለም ፍጻሜ በዘመኑ ሁሉ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ፡፡" (፳፰፥፲፱) ተብሎ የተሰጣቸውን የአደራ ቃልም ሳያጥፉ የዓላውያን ነገሥታትን ተግሣጽና ማሳደድ ሳይሰቀቁ እስከ ሞት ድረስ ታምነው ተገኝተዋል፤ ክርስትናን ለዓለም አዳርሰዋል፡፡

ይህን አደራ የተቀበሉ ከሐዋርያት አባቶቻችንም ትምህርታቸውን በማስቀጠል ውጣ ውረዱን፣ ረኀቡንና ጥሙን፣ በየበረሃው መንከራተቱን፣ ግርማ ሌሊቱን፣ ጸብአ አጋንንቱን፣ ድምፀ አራዊቱን ሁሉ ታግሰው እስከ ዓለም ፍጻሜ በዘመኑ ሁሉ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ ያላቸውን አምላክ ተመክተው አስተምረዋል፡፡ ከሐዋርያት ጀምሮም "በቃል ያለ ይረሳል፣ በመጽሐፍ ያለ ይወረሳል" እንዲሉ አበው መጻሕፍትን ጽፈው ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲሸጋገር አድርገዋል፡፡

ወደ ሀገራችን ኢትዮጵያም ስንመጣ ቀድሞ በሕገ ልቡና ቀጥላም የኦሪቱን ሥርዓት ስትፈጽም የኖረች ነበረች፣ በኋላም ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእናቱ ከቅድስት ድንግል ማርያም እና ከዮሴፍ ጋር ወደ ግብጽ በተሰደደ ጊዜ በኪደተ እግሩ የተጓዘባት፣ ታላላቅ ተአምራትንም ያደረገባት፣ በአራቱም ማዕዘን የባረካት፣ ለሚወዳት እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ዐሥራት አድርጎ ሰጥቷታል፡፡ በሐዋርያትና በሐዋርያውያን አበው ከ፴፬ ዓ.ም ጀምሮ ክርስትና የተሰበከባት እና የተቀበለች ቅድስት ሀገር ናት፡፡ በቀብብሎሽም ዘመንን በዘመን ተክታ ወንጌል እየተሰበከባት ትገኛለች፡፡

ሊቃውንቱ አባቶቻችንም የተረከቡትን ክርስትና በማስፋፋት እስከዚህ ዘመን ድረስ ለማሻገር በየገዳማቱና አድባራቱ ወንበር ዘርግተው ቁጥር ስፍር የሌላቸውን ደቀ መዛሙርት ማፍራት ችለዋል፡፡ ይህም በቀላሉ የተገኘ አልነበረም፡፡ የሚደርስባቸውን መከራ ሁሉ ታግሰው የሚበሉት ምግብ፣ የሚጠጡት ውኃ፣ የሚለብሱት ጨርቅ እያጡ የገቡትን ቃል ኪዳን ጠብቀው፣ ለአምላካቸው ታምነው ፍሬ አፍርተዋል እንጂ፡፡

ዛሬ ዘመን ዘመንን እየወለደ ሥልጣኔው እየተስፋፋ አባቶቻችን ወንበር ዘርግተው ከማስተማር አልፈው ቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን በተለያዩ ቦታዎች ደቀ መዛሙርትን ማፍሪያ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲን ከፍታ በየዓመቱ በርካታ ደቀ መዛሙርትን ታስመርቃለች፡፡ እነዚህ ደቀ መዛሙርት የወንጌል ገበሬ ሆነው በአጭር ታጥቀው የምእመናን ልቡና አለስልሰው፣ የወንጌልን ዘር ዘርተው ፍሬም አብቅለው በወፍና ተምች ከተመሰሉ መናፍቃን ጠብቀው መልካሙን ፍሬ ያፈሩ ዘንድ ቃል አስገብታ ለአገልግሎት ታሰማራለች፡፡

ነገር ግን ከአብነት ትምህርት ቤቶች አስመስክረው የወጡትን፤ ከመንፈሳዊ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጆች የሚመረቁትን ምሁራን በዚህ ዘመን ቤተ ክርስቲያናችን በአግባቡ እየተጠቀመችባቸው ነው ተጠቅማባቸዋለች ለማለት አያስደፍርም፡፡ በተለይም የገጠሪቱ ቤተ ክስቲያንና ምእመናን የተዘነጉ ይመስላሉ፡፡ ለዚህም ማሳያዎችን ማንሳት ይቻላል፡፡

፩.ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን እነዚህን ደቀ መዛሙርት በተለይም በቀን ያስተማረቻቸውን በየቦታው ስትመድብ በአብዛኛው በከተሞችና በዙሪያቸው ላይ ያተኮረ መሆኑን እንደ ችግር ልናነሳው እንችላለን፡፡ ለምሳሌ በአዲስ አበባ እንኳ ባሉት አብያተ ክርስቲያናት ምን ያህል ሰባኪያነ ወንጌል፣ ምን ያህል የአብነት መምህራን፣ ምን ያህል ካህናትና ዲያቆናት ይገኛሉ ብለን ብንጠይቅ የተመጣጠነ ነው ለማለት አያስደፍርም፡፡ ወደ መሐል ከተማ ብንመጣ በአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ዐሥርና ከዐሥር በላይ ሰባክያነ ወንጌል ተመድበው እናገኛለን፡፡ የሠርክ ጉባኤን ትተን በሰንበተ ክርስቲያን ብንመለከት እንኳን በሁለትና ሦስት ወር አንድ ጊዜ እንኳ ላይደርሳቸው ይችላል፡፡ ከአዲስ አበባ በቅርብ ኪሎ ሜትሮች ርቀት ግን አብያተ ክርስቲያናት ቀዳሽ አጥተው፣ ኪዳንና ቅዳሴ በወር እና በዓመት ንግሥ በዓላት ብቻ አገልግሎት የሚሰጥባቸው አብያተ ክርስቲያናት ቁጥራቸው ብዙ ነው፡፡

፪. አብዛኞቹ ኦርቶዶክሳውያን በገጠሩ የሚገኙና በተለያዩ የሥራ መስኮች የተሰማሩ ምእመናን እንደሆኑ ይታወቃል፡፡ ቤተ ክርስቲያንን ይናፍቃሉ፣ ቃለ እግዚአብሔር እንደ ውኃ ጠምቷቸው "የመምህራን ያለህ" እያሉ ይጣራሉ፡፡ በከተማው ሞልተው የተረፉት መምህራን ግን ጥቂት ወጣ ብለው ወንጌልን ለማስተማር ሲቸገሩ እንመለከታለን፡፡ ለመሆኑ ምእመናን እስከ መቼ ቃለ እግዚአብሔር እንደራባቸው ይዘልቃሉ? መቼስ ነው መምህራን የሚደርሱላቸው?

፫.ቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ጀምሮ በመዋቅር የምትመራ መሆኗ ከፍተኛ ጥቅም ያለው ቢሆንም ሊቃውንቱና መምህራኑ ከገጠሩ ይልቅ ከተማውን መምረጣቸው አገልገሎቷን በታቀደለት መሠረት እንዳታከናውን እያደረጋት ይገኛል፡፡ ለዚህም ማሳያው ጉባኤ ቤታቸውን ዘግተው፣ የሚያስተምሯቸውን ተማሪዎች በትነው ወደ ከተማ የሚፈልሱ መምህራን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከቱ መምጣታቸው ነው፡፡

፬. በመምህራን እጥረት ምክንያት ቤተ ክርስቲያን በየገጠሩ የሚገኙ ምእመናንን ለመጠበቅና፣ በእምነታቸውም ጸንተው፣ ንስሓ ገብተው፣ ለቁርባን በቅተው የመንግሥቱ ወራሾች ይሆኑ ዘንድ የምታደርገውን ጥረት ያደናቅፋል፡፡

፭. ቤተ ክርስቲያን በጉያዋ ያቀፈቻቸው ልጆቿ በቃለ እግዚአብሔር እጦት ምክንያት የመናፍቃን ራት በመሆን እየተነጠቁ ይገኛሉ፡፡ ለዚህም ማሳያ የሚሆነን በየዓመቱ የሚወጡ ሪፖርቶች ይህን ያህል ምእመናን አጥተናል እየተባለ ሲቀርብ ማድመጣችንና በተግባርም እያየን መሆናችን ነው፡፡ ስለዚህ ይህን ችግር ለመከላከል ምእመናንን ባሉበት ለማጽናትና አዳዲስ አማንያንን ወደ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እቅፍ ለማስገባት የሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንና ሰባኪያነ ወንጌል፣ የካህናትና ዲያቆናት ድርሻ ከፍተኛ ሊሆን ይገባል፡፡

፮. ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በየጊዜው የምታፈራቸውና የምትመርቃቸው ደቀ መዛሙርትና የአብነት

መምህራን በተገቢው መንገድ በአገልግሎት ባለመመደባቸው ምክንያት ለዘመናት የቀሰሙትን ዕውቀት መጠቀም ተስኖን በተለያዩ ሥራዎች ተሰማርተው የሚገኙ ቁጥራቸው ቀላል አይደለም፡፡ በተለይም የአብነት መምህራንና ተማሪዎች ከቀን የጉልበት ሥራ ጀምሮ ከእጅ ወደ አፍ ኑሮ ሲገፉ መመልከት እየተለመደ መጥቷል፡፡

እነዚህ ከላይ ያነሳናቸው ነጥቦች ብቻ በቤተ ክርስቲያናችን ጎልተው የሚታዩ ችግሮች ናቸው ማለት ባንችልም ከብዙ በጥቂቱ ጎልተው የሚታዩትን እንደ ማሳያ ለመጥቀስ ያህል የቀረቡ ናቸው፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ምን ማድረግ አለብን ብለን ስንጠይቅ ደግሞ ጥቂት የመፍትሔ ሐሳቦችን እናስቀምጥ፡-

፩.ለአብነት መምህራን ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ወንበራቸውን እንዳያጥፉ፣ በርካታ ቁጥር ያላቸው ልጆቻቸውን ሳይበትኑ ባሉበት ሆነው የተምሮ ማስተማር ሂደቱን ማስቀጠል፡፡ ለዚህም ለመምህራኑና ለተማሪዎች ልዩ ድጎማ በማድረግ ለቤተ ክርስቲያን ተተኪ ትውልድ ማፍራት ያስፈልጋል፡፡ ይህም ለገጠሪቱ ቤተ ክርስቲያን ያለው ጠቀሜታ እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ጀምሮ ትኩረት ሊደረግበት ይገባል፡፡

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ባሏት መንፈሳዊ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጆች የሚመረቁ ደቀ መዛሙርት ከዋና ዋና ከተሞች አልፎ በየገጠሩ እየተንቀሳቀሱ ምእመናንን ማስተማር የሚችሉበትን መንገድ በማመቻቸት ከመናፍቃን የቅሰጣ ትምህርት መታደግ፣ የተዘጉና ለመዘጋት የተቃረቡ አብያተ ክርስቲያናትን በማስከፈትና በማጠናከር የድርሻቸውን እንዲወጡ ማድረግ፡፡

፪.የአብነት ትምህርት በማይሰጥባቸው አድባራትና ገዳማት መምህራንን በመመደብ ልጆች ከሕፃንነታቸው ጀምሮ ቤተ ክርስቲያንን እንዲያውቋት፣ድምጿንም እየሰሙ፣ ዕጣኑን እያሸተቱ እና እየቀረቡ ተቀድቶ ከማያልቀው መንፈሳዊ ትምህርቷ እንዲመገቡ በማድረግ ትውልድ የመተካቱን አገልግሎት ማስቀጠል፡፡

፫. ከዚህ ቀደም በከፍተኛ ሁኔታ ተጠናክሮ ቀጥሎ በነበረው የዐውደ ምሕረት ትምህርት ምእመናን በተገቢው መንገድ እንዲያገኙ በመቀስቀስ፣ በቂ ሰባክያነ ወንጌልና መምህራንን በመመደብና ምእመናንን የማጽናት ሥራ ትኩረት ተሰጥቶት መሥራት ያስፈልጋል፡፡ ይህም በየአብያተ ክርስቲያናቱ የሚገኙ መምህራን አገልግሎታቸውን እንዲያጠናክሩና ኃላፊነት እንዲሰማቸው የሚያደርግ በመሆኑ አጠናክሮ ማስቀጠል ያስፈልጋል፡፡

፬. እያንዳንዱ ሀገረ ስብከት በሥሩ የሚመራቸውን የወረዳ ቤተ ክህነትና አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ሰባክያነ ወንጌልን፣ መምህራንና ካህናትን በመመደብ አገልግሎቱንም በመከታተል፣ ችግሮች ሲፈጠሩም አፋጣኝ ምላሽ በመስጠት መብትና ተጠያቂነትን በማስፈን ሂደቱን ማስቀጠል ይገባል፡፡

**ማጠቃለያ፡-**

የሊቃውንት እና የመምህራን መፍለቂያ የሆነችው ቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከዓመት እስከ ዓመት ቃለ እግዚአብሔር የሚነገርባት፣ ኪዳን የሚደረግባት ቅዳሴው የሚቀደስባት፣ አማናዊው የጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም የሚፈተትባት የቅድስና ምንጭ ናት፡፡ ይህንን አገልግሎት ለማፋጠን ደከመኝ ሰለቸኝ የማይሉ አገልጋዮችም ባለቤት ናት፡፡

ነገር ግን የስብከተ ወንጌል እና የአብነት ትምህርት ቤቶች አገልግሎት በአሁኑ ወቅት የሚታየው እንቅስቃሴ በተለይም በገጠሪቱ ቤተ ክርስቲያን የተቀዛቀዘ እና የተዳከመ ሆኗል፡፡ ሁሉም ከተማ ናፋቂ እየሆነ በመምጣቱ የገጠር አብያተ ክርስቲያናት አሁን በአገልጋይ እጥረት ከተዘጉትና በመዘጋት ላይ ካሉት በተጨማሪ ሌሎችም እንዳይከተሏቸው መፍትሔ መሻት አስፈላጊ ነው፡፡ ይህንን ችግር ለመፍታትና ወጥ የሆነ አገልግሎት ለማከናወን ከመንፈሳዊ ዩኒቨርስቲና ኮሌጆች ተመርቀው የሚወጡ ደቀ መዛሙርትም ሆኑ የአብነት መምህራን ለአገልግሎት ሲመደቡ ገጠሩን ታሳቢ ማድረግ ስለሚያስፈልግ የሚመለከተው አካል ትኩረት ሰጥቶ ሊሠራበት ይገባል፡፡

***ወስብሐት ለእግዚአብሔር***

# የተማሩና ጸሎተኛ የቤተ ክርስቲያንን ችግሮች ለማቃለል ዕለት ዕለት የሚተጉ ታላቅ አባት

ክፍል ሁለት

በካሳሁን ለምለሙ

***የተወደዳችሁ አንባብያን የዚህን ጽሑፍ የመጀመሪያ ክፍል ከዚህ በፊት በነበረው እትም ላይ ማቅረባችን ይታወሳል። ሁለተኛውንና የመጨረሻውን ክፍል ደግሞ እነሆ።***

በተጨማሪም አሁን የቅዱስ ፊልጶስ ካቴድራል የተሠራበት ቦታ በዘመኑ የመከላከያ ኮንስትራክሽን ድርጅት (መኮድ) የሥራ ኃላፊዎች የመኖሪያ ቤት መሥሪያ እንዲሆን ሲደረግ ምእመናን አቶ ወልዱ ተዘራ፣ አቶ ሰይፉ እግዚኦ፣አቶ ሙሉጌታ በቀለ፣ አቶ ገብረ ሕይወትና ሻምበል ኃይሉ የተባሉ ምእመናንን አስተባብረው ይዞታውን በማስከበር በአንድ ቀን በቦታው መቃኞ ቤት በእንጨትና በጭቃ አሠርተው ታቦተ ሕጉን በማስገባታቸው ሕይወታቸውን የደኅንነት አደጋ ውስጥ እስከ መግባት ድረስ ነበር።

ከዚያ በኋላም አገልግሎታቸውን በትክክል የሚያውቁላቸው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ዓረፍተ ዘመን ስለገታቸውና ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛውም ከኃፊነታቸው ስለተነሡ ጉዳዩ ከቀደመው በበለጠ የፖለቲካ ትርጉም ተሰጥቶት በከባድ ሁኔታ ውስጥ ቢሆኑም ትግላቸውን አላቆሙም ነበር። ያደርጉት የነበረው ቤተ ክርስቲያን ተኮር ትግል ትክክል ቢሆንም በተነሳው የፖለቲካ ጉዳይ በመስጋት ወደ ጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤተ ክርስቱያን እንዲዛወሩ ተደርጓል።

ወደ ጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን በ፲፱፻፷ ዓ.ም ከተዛወሩ በኋላ ከካህናትና ከምእመናን ጋር በቀላሉ በመግባባት የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት በማስጠበቅ፣ የጎደሉ ንዋያተ ቅድሳትና በማሟላት እውነተኛ አገልጋይና የመንጋው እረኛ መሆናቸውን አስመስክረዋል። በዚህ የበቃና የነቃ አገልግሎታቸው በተመደቡ በአንድ ዓመታቸው ምስጉን አገልጋይ በሚል ሽልማት ተበርክቶላቸዋል።

በ፲፱፻፹፫ ዓ.ም ነሐሴ ወር ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ (የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ



መልአከ ብርሃናት ዘመንፈስ ቅዱስ ገብረ አምላክ

ክርስቲያን ፓትርርክ) በዘመኑ የነበረው መንግሥት ከመንበራቸው ሲያሳድዳቸው በመንበራቸው ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ ዓቃቤ መንበር ሆነው በተሾሙበት ወቅት የመልአከ ብርሃን ዘመንፈስ ቅዱስን ትጋት ስለሚያውቁ ከመስከረም ወር ፲፱፻፸ ዓ.ም ጀምሮ የደብረ ምጥማቅ ቅዱስ ፊልጶስ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ሆነው ተሹመዋል። በዚያ ወቅት ማለትም በ፲፱፻፱ ዓ.ም የንስሓ ልጆቻቸውንና ሰበካ ጉባኤውን በማስተባበር የቤተ ክርስቲያኑን ወሰን በማስከበር ዙሪያውን በግንብ አጥር አሳጥረዋል። በተጨማሪም በየጊዜው ቤተ ክርስቲያን በምታዘጋጃቸው መርሐ ግብራት ሁሉ ጥሪ እየተደረገላቸው በመሳተፍ ስለ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎትና ስለ ምእመናን ሁኔታ ሐሳብ አስተያየት ይሰጡ ነበረ።

አባታችን መልአከ ብርሃናት ዘምንፈስ ቅዱስ በተለያዩ አድባራት በመዘዋወር ከሰጡት አገልግሎት መካከል በጽርሐ ንግሥት ፋሪ ቅድስት ሐና ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ ሆነው በተመደቡበት ወቅት የደብሩን

ታሪካዊነት የሚመጥኑ በርካታ ሥራዎችን ሲሠሩ ቆይተዋል። ደብሩ በወይዘሮ ሥኂን ሚካኤል ርስት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ እና የእቴጌ መነን፣የአጼ ኃይለሥላሴ፤ ከፋስሽት ጣሊያን የተማረኩ ቅርሶች በውስጡ ስለሚገኙ ቅርሶች እንዲጠበቁና እንዲመዘገቡ ዘመናዊ የዕቃ ግምጃ ቤት እንዲኖረው አድርገዋል።

ከዚህ በተጨማሪም ካህናቱ ለመተዳደሪያ የሚሆናቸው ወርኃዊ ገቢ እንዲኖራቸውም ከአካባቢው ባለመሬቶች (ባለጸጎች) ጋር በመነጋገር የእርሻ መሬት እንዲታረስላቸው አድርገዋል። ከእርሻው የተገኘውንም ምርት ካህናቱ ለወርኃዊ ቀለብ የጠበቅበት ነበር። በተጨማሪም የመካኒሳ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አዲስ የነበረበት ወቅትና ሕዝብ ያልሰፈረበት ሥፍራ ስለነበር መሬት ተከራይተው እርሻ በማሳረስ የተገኘውን ምርት ለቤተ ክርስቲያን ገቢ አድርገዋል። ይህ ተግባራቸውም በወቅቱ በዜና ቤተ ክርስቲያን በበቂ ሁኔታ ተዘግቦላቸዋል።

በጽርሐ ጽዮን ሐዋርያትና ጎላ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን በአስተዳደሪነት ሲመደቡ እንዲሁ ደብሩ ለካህናት የሚከፍለው በቂ ደሞወዝ ስላለነበረው የገቢ ምንጭ በማፈላለግ ካህናት ደሞወዝ እንዲያገኙ አድርገዋል። ደብሩ በንጉሡ ዘመን ከተደረገለት ጥገና በኋላ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ሕንጻ ቤተ ክርስቲያኑን በማሳደስ አስመርቀዋል። በዚህ የምረቃ ሥነ ሥርዓት ወቅት ለፈጸሙት አገልግሎት ካህናትና ምእመናን በጋራ ሆነው ሙሉ የመቀደሻ ልብሰ ተክህኖ ከነአክሊሉ፣ መቀደሻ የብር መስቀልና የብር አይከን ሸልመዋቸዋል።

ከጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ፊት ለፊት የሚገኘውንና ያለአግባብ ተወስዶ የነበረውን የደብሩን ይዞታ ራሳቸው ፍርድ ቤት እየተገኙ በመከራከር የደብሩን ወሰን አስመልሰዋል። ቦታውን አሁን ደብሩ ትልቅ ሕንፃ እየገነባበት ይገኛል። መልአከ ብርሃናት ዘመንፈስ ቅዱስ ገብረ አምላክ ከነዚህ አድባራት በተጨማሪ የደብረ ከዋክብት አቡነ አረጋዊ ወገብረ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ይዞታ በማስከበር ለዛሬው ልማት መሠረተ የጣሉ ሲሆን በግል እና በዕድር ተይዘው የነበሩ የደብሩን የመቃብር ቦታዎች ጭምር አስመልሰዋል።

በደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስትያን ለአገልግሎት በተመደቡበት ወቅትም የደብሩ የሙዳየ ምጽዋት ገቢ ከአንድ ሚልዮን ብር በላይ ብልጫ እንዲያሳይ ያደረጉ ሲሆን ለብዙ ዓመታት በግለሰብ ተይዞ የቆየውን የጸበል ቦታ እንዲከበር በማድረግም የማይረሳ ሥራ ሠርተዋል። በተጨማሪም በሊዝ የተገኘው የብሥራተ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ዘመናዊ ትምህርት ቤት የተሠራበት ቦታ የሊዝ ኪራይ ባለመከፈሉ ውሉ ተሰርዞ ወደመሬት ባንክ እንዲገባ በተወሰነበት ወቅት ደርሰው በአጭር ጊዜ ውስጥ ስምንት ሚልዮን ብር በመክፈል ቦታውን ከመወረስ አድነዋል።

በደብረ ሰላም ቅዱስ እስጢፋኖስ ቤተ ክርስቲያን፤ በደብረ ገሊላ ቅዱስ አማኑኤል ካቴድራል፤ በደብረ ነጎድጓድ ቅዱስ ዮሐንስና ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን፤ በደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ፤በደብረ ቀራንዮ መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን በቤተ ክርስቲያኗ ውሳኔ መሠረት ተዘዋውረው በቅንነትና በታማኝነት ልዩ ልዩ አገልግሎት ሰጥተዋል። መልአከ ብርሃናት ዘመንፈስ ቅዱስ ገብረ አምላክ በጣም ደፋር፤ ግልፅ፤ፊት ለፊት የሚናገሩ፤ ዝቅተኛ ሥራ ለሚሰሩና ለተገፉ ምእመናን ወገኖቻቸው የሚወግኑ፤ አለአግባብ ለሚሰጡ የባለሥልጣናት ውሳኔዎች መልስ የሚሰጡ፤ እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና መብት የማይደራደሩ አባት ነበሩ።

ከቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ውጭ የሆነ ባሕርይን ያሳየ አገልጋይን የማይታገሡ አባት ከመሆናቸውም በላይ የቤተ ክርስትያንን ሀብት አባክኗል ብለው የሚያስቡትን ሰው እንኳን ዝም አይሉም ነበር። በቤታቸው እንግዳ ተቀባይና ደግ የትሕትና አባት ነበሩ። ሊቃውንትን የሚከብሩና የሚያደንቁ አባት እንደነበሩም ይታወቃል። የተማሩና ጸሎተኛ ብቻ ሳይሆኑ የቤተ ክርስቲያንን ችግሮች ለማቃለል ከፍተኛ ጥረት ያደርጉ የነበሩ አባትም ነበሩ። መኖሪያ ቤታቸው ሳይቀር የተቸገሩና የተበደሉ ካህናትና መምህራን ማረፊያ ነበር።

በአገልግሎት ዘመናቸው ቄስ፤ ቄሰገበዝ፤ መምህር፤ መልአከ ብርሃናት፤ መልአከ ገነት፤ መልአከ ሰላም፤ ሊቀ ብርሃናት የሚሉ የመዓርግ ስሞች ተሰጥቷቸዋል። ነገር ግን እርሳቸው መልአከ

ብርሃናት በሚለው መጠሪያቸው ጸንተው ቆይተዋል። መልአከ ብርሃናት ዘመንፈስ ቅዱስ ገብረ አምላክ ከ፲፱፻፶፬ ዓ.ም ጀምሮ በሕግ ካገቧቸው ባለቤታቸው ወይዘሮ አስካለ ማርያም ዓባይ ጋር በሞተ ሥጋ እስከተለዩበት ጊዜ ድረስ ለስልሳ ዓመታት በትዳር አብረው የኖሩ ሲሆን አንድ ወንድና ሥድስት ሴት ልጆችን አፍርተዋል። አሥራ አንድ የልጅ ልጆችንም አይተዋል። መልአከ ብርሃናት ዘመንፈስ ቅዱስ ገብረ አምላክ በዕድሜአቸው መጨረሻ ሕማመ ሥጋ ገጥሟቸው ለተወሰነ ጊዜ በሕክምናና በጠበል ሲረዱ ቆይተው በመጨረሻም ሚያዝያ ፲፮ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም በጌታችን በአምላካችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ በዓል ዕለት በተወለዱ በሰማንያ ስድስት ዓመታቸው ከዚህ ዓለም ድካም ዐረፈዋል። ባለቤታቸው፣ልጆቻቸውና የልጅ ልጆቻቸው፣ ብፁዓን አበው ሊቃነ ጳጳሳት እንዲሁም በርካታ ካህናትና ምእመናን በተገኙበት በመልዕልተ አድባራት ደብረ ቀራንዮ መድኃኔ ዓለም ገዳም ሚያዝያ ፲፯ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ሥርዓተ ቀብራቸው ተፈጽሟል።›

ዝግጅት ክፍላችንም ከአባታችን በረከት ይክፈለን እያለ ከአባታች ሕይወትና የአገልግሎት ዘመን ብዙ ቁም ነገር ልንማር እንደሚገባ ያምናል። አባታችን በሕይተ ሥጋ በዚህች ምድር ላይ በነበሩበት ወቅት እግዚአብሔርን የሚያስደስተውን ሰው የሚፈልገውን ሥራ ሠርተው አልፈዋል። የሰው ልጅ በዘመኑ እግዚአብሔር የሚወደውን መልካም ሥራ ሰርቶ ማለፍ ቢችል በምድር ቆይታው ያጣውን ነገር በሰማይ የጽድቅ አክሊልን ይቀዳጃል። መልካም ሥራ መልሶ ይከፍላልና የዘመኑ ወጣቶች ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎትና ለመልካም ሥራ ብትፋጠኑ ለሕዝብና ለሀገር ትልቅ በረከቶች ትሆናላችሁ።

ቤተ ክርስቲያንን በቅንነትና በታማኝነት ማገልገል ከምናገኘው ጸጋና በረከት በተጨማሪ ሰዎች በእኛ መልካም ሥራና አገልግሎት ሲለወጡ ማየት ወይም በቀናው መንገድ ሲጓዙ መመልከት የሚሰጠው መንፈሳዊ ርካታ የላቀ ይሆናል። በእርግጥ አገልይነት ከእግዚአብሔር የሚሠጥ ጸጋ ነውና እውነተኛ አገልጋይ ለመሆን ራስን ለፈጣሪ ማስገዛትና በዕውቀት፣በትሕትና፣በታዛዥነት መስመር መጓዝ አስፈላጊ ነው።

አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያናችን አገልጋዮች እውነተኛ አገልጋይ ቢሆኑም አንዳንዶች ደግሞ ለአገልግሎት ሳይሆን ራስን በንዋይ ለማበልጸግና የተደላደለ ወይም የተመቻቸ ኑሮ ለመኖር የሚመኙ በመሆኑ ከአገልግሎቱ ይልቅ የራሳቸውን የምቾት ደኅንነት የሚያስጠብቁ ናቸው። ከአባታችን መልአከ ብርሃናት ዘመንፈስ ቅዱስ ገብረ አምላክ የአገልግሎትና የሕይወት ጉዞ ግን በርካታ ቁም ነገሮችን የምንማር ሲሆን የቀደሙ አባቶቻችን ለአገልግሎት የሚሠጡት ትኩረት አሁን ካለው የዘመኑ ትውልድ ጋር ሲነጻጸር የሰማይና ምድር ያህል ርቀት ያለው መሆኑን እንገነዘባለን። የቀደሙ አባቶቻችን ለንዋይና ለዝና እጅ ሳይሰጡ የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎት ብቻ ማእከል አድገው ሲያገለግሉ የኖሩ ነበሩ። ስለዚህ የዚህ ዘመን ትውልድ የቀደሙ አባቶቻችንን የአገልግሎት ፈለግ በመከተል በእውነተኛ አገልጋይነት ስሜት ቤተ ክርስቲያንና ምእመናናን ማገልገል ይገባዋል።

ቤተ ክርስቲያን በዘመናችን ታይቶ በማይታወቅ ፈተና ውስጥ ባለችበት በዚህ ወቅት በዚህ ዘመን ያለን ሰዎች የቤተ ክርስቲያንን ሸክም ማቃለል ለሚገጥሟት ውጫዊና ውስጣዊ ፈተናዎች አፋጣኝ ምላሽ መስጠት ተግቢ ብቻ ሳይሆን ሃይማኖታዊ ግዴታችንና በሰማይ የሚያስጠይቀን መሆኑን መረዳት ይኖርብናል። ትግል እዚህ የደረሰችውን ቅድስት ቤተ ክርስቲያንናችንን ለመጪው ትውልድ የማስተላለፍ ታሪካዊና ሃይማኖታዊ አደራ አለብን። ይህንን አደራ ለመወጣትም ጥረት ማድረግ የሁላችንም ድርሻ ሊሆን ይገባል። በእውነት የሚያገለግሉ የቤተ ክርስቲያን አሁንም ድረስ መኖራቸውን በተለይ ወጣቶች ተረድተው ከአባቶቻችን እግር ሥር ተቀምጠው ስለእውነተኛ አገልጋይነትና አገልግሎት ሊማሩ ይገባል። በተለይ የቤተ ክርስቲያናችን አስተምህሮ በዓለም ዙሪያ ተዋውቋል የሚል እምነት ስለሌለን ወጣቱ ትውልድ ዓለም በሚጠቀምባቸው ቋንቋዎች ሁሉ ዘመኑ በወለደው ቴክኖሎጅ በመታገዝ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባዘዘን መሠረት ስብከተ ወንጌልን ለዓለም ሁሉ ማዳረስ ያስፈልጋል።

# በመላው ዓለም ያሉ ኦርቶዶክሳውያን ለአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ዘብ መቆም አለባቸው

ክፍል ሁለት

በካሣሁን ለምለሙ

*የተወደዳችሁ አንባብያን የዚህን ቃለ መጠይቅ የመጀመሪያ ክፍል ባለፈው እትማችን ላይ ማቅረባችን ይታወሳል፡፡ በዚህ እትማችን ደግሞ ክፍል ሁለትን ይዘንላችሁ ቀርበናል፡፡ በጥሞና ትከታተሉ ዘንድ ግብዣችን ነው፡፡*

**ስምዐ ጽድቅ፡- የስልጤ ዞን ለዘመናት እስላማዊ አክራሪነት የነገሠበት በመሆኑ የቤተ ክርስቲያንንና የምእመናንን ክብርና መብት ለማስጠበቅ የተቀመጠው የመፍትሔ አቅጣጫ ምንድን ነው?**

**ሊቀ ኅሩያን ቆሞስ አባ ዮሴፍ፡-** ቤተ ክርስቲያንና ምእመናን ከእግዚአብሔር በታች ሀገሪቱን የሚመራው መንግሥት "ሰላምና ደኅንነታችንን ከአክራሪዎች ይጠብቅልናል" የሚል እሳቤ አላቸው፡፡ ይህም በመሆኑ ነው የደረሰውን መከራ ችለን ከፌዴራል፣ከክልልና ከዞኑ ከመጡ የመንግሥት አመራሮች በተገኙበት በተደረገ የውይይት መርሐ ግብር ላይ የስልጤ ዞን ሃይማኖታዊ አክራሪነት የሚበዛበት መሆኑ ከዚህ ቀደም ያለማቋረጥ ኦርቶዶክሳውያን በጭካኔ የሚጨፈጨፉበት እና አብያተ ክርስቲያናት የሚቃጠሉበት አካባቢ መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ እንዲያስገቡ አስረድተናቸዋል፡፡

የስልጤ አክራሪ ሃይማኖተኞች በተደጋጋሚ በምእመናን ሕይወት፣ ሀብትና ንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሱ መሆኑን ለሚመለከታቸው የመንግሥት አመራሮች ስናመለክት ብንቆይም እስካሁን ድረስ መፍትሔ እንዳላገኘን ለአመራሮቹ በድጋሜ ነግረናቸዋል፡፡ ሁልጊዜ ለጉዳዩ መፍትሔ ሳይሰጥ የሚታለፍ ከሆን ለሀገር አንድነት እንቅፋት እንደሚሆን አስረድተን ስለሆነም አሁን ለተፈጸመው ወንጀል መፍትሔ እንዲሰጠውና ለወደፊቱም መንግሥት የአካባቢውን ምእመናን ደኅንነት ለመጠበቅ ምን እቅድ እንዳለው በግልጽ እንዲነገረን ጠይቀናል፡፡

የመንግሥት አመራሮቹም በእኛ በኩል የሚጠበቅብንን ሁሉ እንወጣለን እናንተ የሃይማኖት አባቶችና ሕዝቡ ደግሞ የሚጠበቅባችሁን ኃላፊነት ተወጡ የሚል ሐሳብ በምክክር መድረኩ አንሥተዋል፡፡ ሕዝቡና የሃይማኖት አባቶች የሚጠበቅባቸውን ቢወጡም መንግሥት ግን ፀጥታን የማስፈንና ሰላምን የማረጋገጥ ኃላፊነቱን እየተወጣ እንዳልሆነ አስረድተናል፡፡ ሰሞኑን በምእመናን በቤተ ክርስቲያን ላይ ክፍተኛ ወንጀል የፈጸሙ አክራሪ እስላሞች ላይ ተመጣጣኝ ሕጋዊ ርምጃ በመውሰድ መንግሥት የሕግ የበላይነት መረጋገጡን እንዲያሳይ ፍላጎታችን መሆኑን አስረድትን በጉዳዩ ዙሪያም ክትትልና ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ መሆናችንን ተናግረናል፡፡ ከቀበሌ እስከ ዞን ድረስ



ሊቀ ኅሩያን ቆሞስ አባ ዮሴፍ ደስታ
(የሀድያና ስልጤ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ)

ያሉ የመንግሥት አመራሮች በፈጸሙት ወንጀል ልክ ተገቢው ቅጣት ካላገኙ ሌላ ጊዜም ተመሳሰይ ወንጀል ላለመፈጸማቸው ምንም ዓይነት ዋስትና ያለመኖሩን አስረድተናል፡፡

በዞኑ የሚፈጸመው ሃይማኖት ተኮር ጥቃት ምንጩ ተጣርቶ ድርጊቱንም የሚያባብሱና የሚያቀናብሩ የአካባቢው የመንግሥት አመራሮች ላይ ተከታታይ የሆነ የማያዳግም ርምጃ በመውሰድ የቤተ ክርስቲያንና

የምእመናን ደኅንነት በዘላቂነት እንዲረጋገጥ በሀገረ ስብከት ደረጃ የመፍትሔ አቅጣጫ አስቀምጠናል፡፡ በውይይቱ ላይ ወንጀሉ ተወግዟል፣አብተ ክርስቲያናት በጋራ እንዲሠሩ ተወስኗል፤የተጎዱ ምእመናን እንዲካሱና እንዲጽናኑ ይደረጋል፤ እንዲሁም የወደሙና የተቃጠሉ ሀብት ንብረቶች የሚተኩበት መንገድ እንደሚፈለግ ተነጋግረናል፡፡ ከታች ጀምሮ ያሉ አጥፊዎች ሁሉ ወደ ሕግ እንደሚቀርቡ ከስምምነት ላይ ደርሰናል፡፡ ጉዳዩ ትኩረት እንዲያገኝና ዘላቂ መፍትሔ እንዲመጣም ሀገረ ስብከቱ ከፌዴራል እስከ ዞን ካሉ የመንግሥት አመራሮች ጋር ተከታታይ የሆነ ውይይት ለማድረግ ዕቅድ ይዘናል፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በቤተ ክርስቲያንና በምእመና ላይ የደረሰው ጉዳት በዝርዝር ይፋ የሚሆነው መቼ ነው? በአካባቢው እየደረሰ ያለውን ጉዳትስ ለመከላከል ቤተ ክርስቲያን መሥራት ያለባት ምንድን ነው ይላሉ?**

**ሊቀ ኅሩያን ቆሞስ አባ ዮሴፍ፡-** በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ የደረሰውን ሃይማኖት ተኮር ጥቃት አስመልክቶ የመጀመሪያ ዙር የዳሰሳ ጥናት አካሄደናል፡፡ የዳሰሳ ጥናቱ የተጀመረው በሳንኩራ ሲሆን በሳንኩራ የሚኖሩ ኦርቶዶክሰውያን ጠንካሮች በመሆናቸው መከራውን ተቋቁመው ጥናት አጥንተው ልከውልናል፡፡

አሁን የቀረው ወራቤ፣ጭንጮና ሌሎች አካባቢዎች ናቸው፡፡ ጥናቱን የመንግሥት አመራሮች ለማጥናት ሐሳብ ያቀረቡ ቢሆንም ሀገረ ስብከቱ ባቋቋመው የጥናት ግብረ ኃይል ብቻ እንደሚከናወን በማስረዳት ተማምነን ጥናቱን በአሁኑ ሰዓት በራሳችን እያካሄድን እንገኛለን፡፡ ይህ የዳሰሳ ጥናት ስለሆነ በቀጣይ ጥልቅ የሆነ ጥናት በማጥናት ለሚዲያና ለመንግሥት አካላት የሚሆነውን መርጃ ለይተን እናቀርባለን፡፡ ጥቃቶችን ከመከላከል አንጻር በቤተ ክርስቲያን ደረጃ የተቀናጀና የተናበበ ሥራ የመሥራት ጉድለቶች ይስተዋላሉ፡፡ የተቀናጀ ሥራ ባለመሠራቱና ሁላችንም በየአቅጣጫው በመሮጣችን ምክንያት ቤተ ክርስቲያናችንና ምእመናን ከጊዜ ወደጊዜ ለከፋ ችግር ተጋላጭ ሆነዋል፡፡ ይህም በመሆኑ የሀድያና ስልጤ ሀገረ ስብከት የነበረውን ቤተክህነታዊ አደረጃጀት በሚገባ አጠናክሮ የሚንቀሳቀስ ይሆናል፡፡ በዚህም በቤተ ክርስቲያንና በምእመናን ላይ የሚደርሰውን ጥቃት ቀድመን የመከላከል ሥራዎችን እንሠራለን፡፡ መዋቅራዊ አደረጃጀቶቻችንን አጠናክረን አጥቢያ ድረስ በመውረድ በየጊዜው ክትትልና ድጋፍ እናደረጋለን፡፡ የምእመናንን የኑሮ ሁኔታ፣ ደኅንነታቸውን እንዲሁም የአገልጋዮችንና የአብያተ ክርስቲያናትን ሁኔታና ደኅንነት የምንከታተል ይሆናል፡፡ ከየወረዳ ቤተ ክህነቱ ከሚቀርብ ወቅታዊ ሪፖርት ባሻገር በሀገረ ስብከት ደረጃ የአገልዮችን፣የምእመናንንና የአብያተ ክርስቲያናትን ሁኔታ በየጊዜው በመገምገም መልካም ነገሮችን ማስቀጠል ጉደለቶችን የመሙላት ችግሮች ደግሞ በፍጥነት እንዲታረሙ የማድረግ ሥራ ከመሠራቱ ባሻገር ችግሮች እንዳይፈጠሩ የቅድመ መከላከል ሥራዎችን የምንሠራ ይሆናል፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በጥቃቱ የተጎዱ ምእመናንና አገልጋዮችን ለማጽናናት ሀገረ ስብከቱ ምን እየሠራ ነው ?**

**ሊቀ ኅሩያን ቆሞስ አባ ዮሴፍ፡-** የተፈናቀሉ አገልጋዮችንና ምእመናንን ወደ አካባቢያቸው የመመለስ ሥራ ከተሠራ በኋላ በቀጥታ በተለያየ መንገድ የማጽናናት ሥራ የምንሠራ ይሆናል፡፡ የሀድያና ስልጤ ሀገረ ስብከት ምእመናንና አገልጋዮችን ለማጽናናት ከተለያዩ አካባቢዎች የጉባኤ እናዘጋጅ ጥያቄዎች እየቀረቡልን ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በሀገረ ስብከቱ የተጎዱ ምእመናን የሚረዱበት የባንክ ሒሳብ ቁጥር ከፍተን ልዩ እንቅስቃሴ እያደረግን ነው፡፡ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ያሉ ኦርቶዶክሳውያንና ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን የሚችሉትን ያህል እገዛ እንዲያደርጉም ጥሪ አስተላልፈናል፡፡ በሚሰበሰበው ገንዘብ የተጎዱ ምእመናን ይካሱበታል፤ የፈረሱ አብያተ ክርስቲያናትና ወደመው ሀብት ንብረት ይተካበታል፤ ብለን በማሰብ ነው ይህንን የባንክ ሒሳብ የከፈትነው፡፡

ጉባኤያት ቶሎ ቢደረጉ መልካም ነው፤ ነገር ግን በየአጥቢያው ጉባኤ ከመደረጉ በፊት የተቃጠሉ አብያተ ክርስቲያናት መቃኞ ከተሠራላቸው በኋላ ቢሆን የበለጠ ጥሩ ነው፡፡ ጉባኤ ለማድረግ ሲታሰብ ቢያንስ ጸሎት የሚደረግበት መቃኞ ቤት ያስፈልጋል፡፡ ጉባኤ አዘጋጆቹም ቤተ ክርስቲያን የመታወቃቸውና ከቤተ ክርስቲያን ጥቅም ይልቅ ለግለሰብ ጥቅም ቅድሚያ የማሰጡ እንዳይሆኑ ጥንቃቄ የተሞላበት ሥራዎችን መሥራት ግድ ይላል፡፡ በቀጣይ በጉባኤም ሆነ በሌሎች ሁኔታዎች የተሰበሰበ ሀብት ወደ አንድ

ማእከል ገብቶ የተጎዱ ምእመናን የሚጠገኑበት የተቃጠሉት አብያተ ክርስቲያናት የሚገነቡበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡ ሀገረ ስብከቱ መሥራት ያለበትን ሥራ ከጨረሰ በኋላ ጉባኤያትና መሰል መርሐ ግብራት መቼ እንደሚደረጉ መግለጫ የምንሰጥ ይሆናል፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በስልጤ ዞን በአብያተ ክርስቲያናትና በምእመናን ላይ በተደጋጋሚ እየተፈጸመ ያለውን ጥቃት ኢትዮጵያውያንና የዓለም ሕዝብ እንዲረዱት የሚዲያ አጠቃቀማችሁ ምን ይመስላል?**

**ሊቀ ኅሩያን ቆሞስ አባ ዮሴፍ፡-** ሰዎች በስልጤ ዞን የተፈጸመውን ጥቃት አቅልለውና ዋጋውን አሳንሰው እንዳይመለከቱት የተለያዩ የብዙኃን መገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ኢትዮጵያውያን ብሎም የዓለም ማኅበረሰብ እንዲያውቁት በርካታ ሥራዎችን ሠርተናል፡፡ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ሕርያቆስ ብቻ ብዙ ደክመዋል፡፡ ይህ ግን ከችግሩ አንጻርና ልነሠራ ካሰብነው አኳያ ሲታይ በሚዲያ አጠቃቀም ዙሪያ ያልሠራናቸው እንዳሉና ገና ብዙ የቤት ሥራዎች እንዳሉብን ተገንዝበናል፡፡ ቤተ ክርስቲያን ባሏት የሚዲያ አማራጮች ሁሉ ሰሞኑን የተፈጸሙ ጥቃቶችን የተመለከቱና ተገቢ የሆኑ መረጃዎችን እያስተላለፍን እንገኛለን፡፡ የተጋነነ መረጃ ሳይሆን እውነተኛና የጉዳቱን መጠን ብቻ የሚያሳይ ዘገባዎች እንዲዘገቡ ለበርካታ ጊዜያት መረጃዎችን ለሚዲያ አካላት ሰጥተናል፡፡

ይሆን እንጂ አንዳንዶቹ ጉዳዩን አጋነው ሌሎቹ ደግሞ ችግሩን አንኳሰውና አጣጥለው ዘግበውታል፡፡ ይህ ኢ-ሚዛናዊ የሆነ አካሄድ ማንንም አይጠቅምም፡፡ በቤተ ክርስቲያናችን መዋቅሮች ሥር ያሉ የሚዲያ አማራጮች በቤተ ክርስቲያን የሚደርሰውን መከራ ለመዘገብ ከፍተኛ የሆነ ዳተኝነት ይታይባቸዋል፡፡ ጠላቶቻችን በጣም ርቀውን ከመሄዳቸው ባሻገር በሚዲያዎቻቸው እውነቱን ሀሰት ሀሰቱን እውነት እያደረጉ በማቅረብና ተከታዮቻቸውን እያደናገሩ በቤተ ክርስቲያንና በምእመናና ላይ ከፍተኛ የጥፋት ዝናብ እንዲዘንብ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ሚዲያን የምንጠቀመው ፍትሕ ያላገኘ ፍትሕ እንዲያገኝ እንጂ የተሳሳተና የተንሸዋረረ መረጃ የሚቀርብበት ስላልሆነ ሀገረ ስብከቱ ከበፊቱ የተሻለ የሚዲያ አጠቃቀም ይኖረዋል፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- በመጨረሻ ቤተ ክርስቲያን ካለችበት ወቅታዊ ሁኔታ አንጻር የሚያስተላልፉት መልእክት ምንድን ነው?**

**ሊቀ ኅሩያን ቆሞስ አባ ዮሴፍ፡-** አሁን በሀገራችን ሁሉም ነገር ተስፋ የሚያስቆርጥ ይመስላል፣ እኛ ግን ክርስቲያኖች ነንና በሀገራችን ላይ ለደቂቃም ቢሆን ተስፋ መቁረጥ ለብንም፡፡ በተለይ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮች በሃይማኖታችን ጸንተን በመኖር በሚመጣው የመከራ ወጀብ ሁሉ በቀላሉ የምንናወጥ ሰዎች መሆን የለብንም፡፡ መከራዎች ይመጡ ዘንድ ግን መሆኑን ተረድተን በዚያ መከራ ውስጥ ለማለፍ መትጋት ያስፈልጋል፡፡ መከራ ባለበት ሁሉ ለመጽናትና መከራ መስቀሉን ለመሸከም መዘጋጀት ያስፈልገናል፡፡

አንዳንዶች በሚኖሩበት አካባቢ አክራሪዎች መከራ ሲያበዙባቸው መከራን መጋፈጥ ያቅታቸውና ከልጅነት እስከ ዕውቀት ያፈሩትን ሀብት ንብረት ትተው ስደትን ምርጫቸው ያደርጋሉ፡፡ ይህ ከሆነ የስደታችን መቆሚያው የት ነው? ጸንተን እውነቱን ካልተጋፈጥን እኮ በተሰደድንበት አካባቢም ሌላ ስደት ይመጣል፡፡ ይህ እውነታ ደግሞ በሀገራችን ኢትዮጵያ እየተፈጸመ እያየነው ነው፡፡ ስለሆነም መበርታት፣መጽናትና መከራን ለመቀበል መዘጋጀት ይኖርብናል፡፡ አምላካችን እግዚአብሔርም ቸር አምላክ ነውና የመከራውን ጊዜ አያስረዝብንም፡፡

የትም ያሉ ስለሆነም በየትኛውም ዓለም የሚገኙ ኦርቶዶክሳውያን ምእመናን በሃይማኖታቸው ታምነውና ጸንተው እንዲኖሩ፣ ለአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያያናቸውም ዘብ መቆም እንዳለባቸው፣ በየትኛውም አካባቢ ያለን ኦርቶዶክሳውያን ያለንን አቅም አሟጠን በመጠቀም የቤተ ክርስቲያንና የምእመናን ደኅንነት የሚጠበቅበትን መንገድ መፈለግ አለብን በማለት አባታዊ መልእክቴን አስተላለፋለሁ፡፡

**ስምዐ ጽድቅ፡- ለነበረን የስልክ ቆይታ በእግዚአብሔር ስም አመሰግናለሁ?**

**ሊቀ ኅሩያን ቆሞስ አባ ዮሴፍ፡- እኔም ለተሰጠኝ እድል አመሰግናለሁ፡፡**

# መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ

እህተ ሚካኤል

ልጆች! እንደምን አላችሁ? እግዚአብሔር ይመስገን እኛ በጣም ደኅና ነን፡፡ ትምህርት እንዴት እንዴት ነበር? አሁን የሁለተኛውን መንፈቀ ዓመት የማጠቃለያ ፈተና ጨርሳችሁ አጠናቃችሁ ሰርተፊኬት ለመቀበል



መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ

የዕረፍት ጊዜ ላይ እንደሆናችሁ እናምናለን፡፡ ታዲያ ልጆች! ቀጣዩ የክረምት የዕረፍት ጊዜያችሁን ዝም ብላችሁ ማሳለፍ የለባችሁም፡፡ በዚህ ክረምት ለቀጣዩ ዓመት የምትማሩትን ትምህርት እንዲሁም የተለያዩ መንፈሳዊ መጻሕፍትን በማንበብ እና ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ ጥሩ ጊዜ ማሳለፍ አለባችሁ፡፡ ጎበዞች!!

ልጆች! ዛሬ የምንነግራችሁ ስለ መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ ታሪክ ነውና በጥሞና ተከታተሉን እሺ ልጆች!

ልጆች! ዮሐንስ ማለት ‹‹ፍስሓ ወሐሴት፤ፍጹም ደስታ›› ማለት ነው፡፡ የመጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስ አባቱ ካህኑ ዘካርያስ እናቱ ደግሞ ቅድስት ኤልሳቤጥ ይባላሉ፡፡ የተወለደውም በሰኔ ፴ (30) ቀን ነው፡፡ ልጆች! ቅዱስ ዮሐንስ መጥምቀ መለኮት የተባለበት ምክንያት ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በ፴ ዓመቱ በዮርዳኖስ ወንዝ ስላጠመቀው ነው፡፡

የመጥምቀ መለኮት አባት እና እናት ካህኑ ዘካርያስና ቅድስት ኤልሳቤጥ እግዚአብሔርን የሚፈሩ መልካም እና ጻድቃን ነበሩ፡፡ ኤልሳቤጥም መካን ነበረችና ልጅ አልነበራቸውም፤ ሁለቱም በዕድሜያቸው አርጅተው ነበር፡፡ እግዚአብሔር ልጅ እንዲሰጣቸው ዘወትር እግዚአብሔርን ይማጸኑ ነበር፡፡ ከዕለታት በአንዱ ቀን ካህኑ ዘካርያስ በቤተ መቅደስ ለማገልገል ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ በማጠን ላይ ነበረ፤ሕዝቡም በውጭ ቆመው ይጸልዩ ነበር፡፤ የእግዚአብሔር መልአክ ቅዱስ ገብርኤል በመሠዊያው ቀኝ ቆሞ ታየው ካህኑ ዘካርያስም የእግዚአብሔርን መልአክ ባየ ጊዜ ደነገጠ ፍርሃትም ወደቀበት፡፡ መልአኩም እንዲህ አለው፦

‹‹ዘካርያስ ሆይ ጸሎትህ ተሰምቷልና አትፍራ ሚስትህ ቅድስት ኤልሳቤጥም ወንድ ልጅ ትወልዳለች ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ፡፡ ተድላና ደስታም ይሆንልሃል ፥ በመወለዱም ብዙዎች ደስ ይላቸዋል፡፡ በጌታ ፊት ታላቅ ይሆናልና የወይን ጠጅና የሚያሰክር መጠጥም አይጠጣም ገና በእናቱ ማሕፀን ሳለ መንፈስ ቅዱስ ይሞላበታል፤ ከእስራኤል ልጆች ብዙዎችን ወደ ጌታ ወደ አምላካቸው ይመልሳል፡፡›› በማለት ነገረው (ሉቃ.፩፥ ፲፫–፲፯)፡፡

ልጆች! ካህኑ ዘካርያስ ለመልአኩ ለቅዱስ ገብርኤል ምን ብሎ የመለሰለት ይመስላችኋል? ዘካርያስ የመልአኩን መልእክት በመጠራጠሩ፦

‹‹እኔ ሽማግሌ ነኝ፥ ሚስቴም በዕድሜዋ አርጅታለችና ይህን በምን አውቃለሁ? አለው፡፡

መልአኩም መልሶ ‹‹ እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ፥ እንድነግርህም ይህችንም የምሥራች እንድሰብክልህ ተልኬ ነበር፤እነሆም በጊዜው የሚፈጸመውን ቃሌን ስላላመንህ ይህ ነገር

እስከሚሆን  ድዳ ትሆናለህ መናገርም አትችልም›› አለው (ሉቃ ፩፥፲፱–፳)

ሕዝቡም በውጪ ሆነው ካህኑ ዘካርያስን እየጠበቁት ነበር በቤተ መቅደስ ውስጥ ከመልአኩ ጋር ሲነጋገር ብዙ በመቆየቱ ተገርመው ነበር። ከቤተ መቅደስ ሲወጣም ከሕዝቡ ጋር መነጋገር አልቻለም፡፡ የሚያናግራቸው በምልክት ብቻ ነበር። በዚህን ጊዜ ካህኑ ዘካርያስ በቤተ መቅደስ ውስጥ ራዕይን እንዳየ አስተዋሉ፡፡ ካህኑ ዘካርያስ የቤተ መቅደስ አገልግሎቱን ሲጨርስ ወደ ቤቱ ሄደ፡፡ ሚስቱም ኤልሳቤጥ ፀነሰች፡፡ ቅድስት ኤልሳቤጥ እጅግ አርጅታ ስለነበር ባለመውለዷ እና መካን በመሆኗ የአካባቢው ሰው ሁሉ ይሰድባት ‹‹ይኽች የማትወልድ መካን›› እያሉ ያሽሟጥጧት ነበር። እግዚአብሔር በፈቀደ ጊዜ ግን ልጅን ፀነሰች፡፡ እርሷም ‹‹ነቀፌታዬን ከሰው መካከል ያስወግድልኝ ዘንድ ጌታ በተመለከተበት ወራት እንዲህ አድርጎልኛል›› አለች (ሉቃ. ፩፥፳፭)፡፡ ከዚያም ለአምስት ወራት ያህል ራሷን ከሰዎች ሰውራ በቤትዋ ተቀመጠች፡፡

ቅድስት ኤልሳቤጥ በፀነሰች በስድስተኛው ወር ዘመዷ የሆነችው የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እናት ቅድስት ድንግል ማርያም ወደ ኤልሳቤጥ ዘንድ ሄደች፡፡ የቅድስት  ድንግል ማርያምን የሰላምታዋን ድምጽ በሰማች ጊዜ በቅድስት ኤልሳቤጥ ማሕፀን የነበረው ፅንስ (ቅዱስ ዮሐንስ) በእናቱ ሆድ ውስጥ በደስታ ዘለለ፡፡ ለቅድስት ድንግል ማርያምና ለልጇ ለኢየሱስ ክርስቶስ ሰገደ፡፡ ሉቃ ፩፥፳፮–፵፩፡፡ በቅድስት ኤልሳቤጥም መንፈስ ቅዱስ ሞላባት፡፡  ድምጿንም ከፍ አድርጋ ‹‹አንቺ ከሴቶች መካከል ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ ፥ የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው፡፡ የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል? እነሆ የሰላምታሽ ድምፅ በጆሮዬ በመጣ ጊዜ ፅንሱ በማኅፀኔ በደስታ ዘሎአልና፡፡ ከጌታ የተነገረላት ቃል ይፈጸማልና ያመነች ብፅዕት ናት›› በማለት እመቤታችን ቅደስት ማርያምን አመሰገነቻት (ሉቃ. ፩፥ ፵፩ - ፵፮)፡፡

ልጆች! ቅድስት ኤልሳቤጥ የመውለጃዋ ጊዜ ሲደርስ ሰኔ ፴ ቀን መጥምቀ መለኮት ቅዱስ ዮሐንስን ወለደችው፡፡  ዘመዶቹም ለተወለደው ሕፃን ስም ሊያወጡለት በአባቱ በካህኑ ዘካርያስ ስም እንዲጠራ ፈልገው ስሙ ‹‹ዘካርያስ›› ይባል ቢሉም ቅድስት ኤልሳቤጥ ግን የለም ‹‹ዮሐንስ›› ነው መባል ያለበት በማለት ነገረቻቸው፡፡ የቅዱስ ገብርኤልን ቃል ባለመቀበሉ ዲዳ የነበረው የሕፃኑ የመጥምቁ ዮሐንስ አባት ዘካርያስም ‹‹ስሙ ማን ይባል?›› ብለው ዘመዶቹ በጠየቁት ጊዜ ብራና እንዲያመጡለት ጠይቆ ‹‹ዮሐንስ›› ይባል ብሎ ጻፈ፡፡ በዚህን ጊዜ አንደበቱ ተፈታለት መናገርም ቻለ፡፡ በቦታው የነበሩት ሰዎችም በሆነው ነገር ሁሉ ተደነቁ፡፡

ልጆች! ካህኑ ዘካርያስም በመንፈስ ተቃኝቶ ‹‹አንተ ሕፃን ሆይ የልዑል ነቢይ ትባላለህ ፥ መንገዱን ልትጠርግ በጌታ ፊት ትሔዳለህና፤ የኃጢአታቸው ስርየት የኾነውን የመዳን ዕውቀት ለሕዝቡ ትሰጣለህ ይህም ከላይ የመጣ ብርሃን በጐበኘበት በአምላካችን ምሕረትና ርኅራኄ ምክንያት ነው፤ ብርሃኑም በጨለማና፤ በሞት ጥላ ተቀምጠው ላሉት ያበራል፤ እግሮቻችንንም በሰላም መንገድ ያቀናል (ሉቃ.፩፥፸፮ ፸፱) በማለት ትንቢት ተናገረ፡፡

ልጆች! መጥምቁ ዮሐንስ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የሚበልጠው ፮ ወር ነው፡፡ ጌታችን በተወለደ ጊዜ ንጉሥ ሄሮድስ የመንግሥቴ ተቀናቃኝ መጣ ብሎ ሊገለው ፈለገ፡፡ በእርሱ የዕድሜ ክልል ያሉትን በተለይም ከሁለት ዓመት በታች ያሉ ሕፃናትን በሙሉ በመሰብሰብ አስገደላቸው፡፡ ቅዱስ ዮሐንስንም ሊያስገድለው ሲል እናቱ ቅድስት ኤልሳቤጥ ይዛው ወደ በረሀ ሸሸች፡፡  የሄሮድስ ጭፍሮችም ሕፃኑ ዮሐንስን ከቤት ባጡት ጊዜ ከቤተ መቅደስ ይኖራል ብለው ወደ ቤተ መቅደስ ሄዱ በደረሱም ጊዜ ሕፃኑ ዮሃንስን ሲያጡ አባቱን ካህኑ ዘካርያስን ቤተ መቅደስ ውስጥ በሰይፍ ገደሉት፡፡

ልጆች ቅዱስ ዮሐንስ እናቱ ይዛው ወደ በረሀ ከሸሸች በኋላ በረሀ ውስጥ መኖር ጀመሩ፡፡ የሰባት ዓመት ልጅ ሳለም እናቱ ቅደስት ኤልሳቤጥ አረፈች፡፡ እግዚአብሔርም ቅዱስ ዮሐንስን አውሬ እንዳይበላው ጠበቀው፡፡ ሲርበው ሰማያዊ ኅብስትን እየተመገበ ሲጠማው ውሃ ከአለት ላይ እየፈለቀለት እየጠጣ የበረሀ አራዊቶች እንደቤተሰብ ሆነውት በበረሀ ውስጥ አደገ፡፡ ልብሱም የግመል ጠጉር ነበረ፤በወገቡም ጠፍር ይታጠቅ ነበረ እስከ ፴ ዓመቱም በበረሃ ኖረ፡፡ ፴ ዓመት ሲሞላውም ‹‹መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሓ ግቡ!›› እያለ እየሰበከ በዮርዳኖስ ዙሪያ ወዳለው አገር ሁሉ ወጣ (ሉቃ.፫፥፫-፮)፡፡ በዚያም ጌታንና መድኃኒታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን አጠመቀው፡፡

ልጆች! ቅዱስ ዮሐንስ ‹‹መጥምቀ መለኮት›› የተባለውም በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የዚህን ቅዱስ አባት ልደት በየዓመቱ ሰኔ ፴ በድምቀት በማኅሌት፣ በቅዳሴ፣ በውዳዜ ታከብረዋለች፡፡

***የመጥምቁ የቅዱስ ዮሐንስ በረከቱ ይደርብን***

# ‹‹የቤተ ክርስቲያን ዩቱዩበሮች›› ነገር!

**ኪኑኪሩ ከአዲስ አበባ**

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምታስተምርባቸውና መረጃ የምትሰጥባቸው ልዩ ልዩ ቅርጽ ያላቸው የመገናኛ ብዙኃን ነበሯት፡፡ ይህም ማለት ቤተ ክርስቲያን መረጃዎችን በጽሑፍ እንዲሁም በቃል በማስተላለፍ ቀዳሚውን ቦታ ትይዛለች ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ፣ ቃለ ወንጌል (ስብከት) ቅኔ፣ እንዲሁም ሌሎች የአብነት ትምህርቶች ሰፊውን ቦታ ይይዛሉ፡፡ ረጅሙን ዘመን ያለፈውም በዚህ መልኩ በጽሑፍና በቃል በሚሰጠው ትምህርትና መረጃ ነው፡፡ ዘመናዊ ዓለም የሚባለው ደግሞ ከጽሑፍና ከቃል ባሻገር ልዩ ልዩ የመገናኛ መሣሪያዎችን ማምረትና ጥቅም ላይ መዋል ሲጀምር ቤተ ክርስቲያንም በሚጠቅማት አግባብ ለመጠቀም ጥረት ስታደርግ ቆይታለች፡፡ ለምሳሌ ሬዲዮ አገልግሎት በኢትዮጵያ ሲጀመር ‹‹የምሥራች ሬዲዮ››ን ለመጠቀም ያደረገችው ጥረት በዚህ ረገድ ሲወሳ የሚኖር ሲሆን ቃለ ወንጌልን ስታስተላልፍበት ቆይታለች፡፡

በጊዜ ሂደት በኢትዮጵያ ከተፈጠሩ የፖለቲካ ለውጦች ጋር ተያይዞ በሃይማኖት እኩልነትና ዓለማዊነት(ሴኪዩላሪዝም) ይስፋፋ ከሚለው አስተሳሰብ ጋር ተያይዞ የሚዲያ ቴክኖሎጂዎችን በሚፈለገው ደረጃ ለመጠቀም ግን አልቻለችም፡፡

በጊዜ ሂደት ግን የሃይማኖት ትምህርቶችና መረጃዎች በሬዲዮና በቴሌቪዝን ሽፋን እንዲያገኙ አንጻራዊ ነጻነት ሲገኝ፣ ከዚያም ባለፈ የሳተላይት ቴሌቪዥኖች መስፋፋት ከመንግሥትም ሕግ በላይ ሆኖ ለክልከላ የማይቻል መሆኑ በአንድም በሌላም መንገድ ቤተ ክርስቲያን የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎችን ለመጠቀም አስችሏታል፡፡

በዚያም መሠረት ቢያንስ ሁለት ቴሌቪዥኖች ማለትም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የቴሌቪዥን ጣቢያ እና የማኅበረ ቅዱሳን የቴሌቪዥን ጣቢያ የቤተክርስቲያን ሆነው ምእመናንን እያገለገሉ ይገኛሉ፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ደግሞ በዓለም ላይ እጅግ እየተስፋፋ ያለው የማኅበራዊ ሚዲያ አማራጭ ሰዎች ሁሉ በነጻነትና በስፋት መረጃ እንዲደርሳቸው ብቻ ሳይሆን እንዲሰጡም እያስቻላቸው ነው፡፡ ሰዎች በቀላሉ ከአንድ የዓለም ማዕዘን ወደ ሌላው ዓለም ማዕዘን መረጃዎችን በፍጥነትና በርካሽ ዋጋ መለዋወጥ ችለዋል፡፡ ከዚህ ተሻግሮም ‹ሰዓት አለፈን› ብለው ሳይሰቀቁ በፈለጉት ጊዜና ሁኔታ ውስጥ መረጃዎችን ለመቀበል ተችሏቸዋል፡፡

ማኅበራዊ ሚዲያ እየሰጠ ካለው ጠቀሜታ ጎን ለጎን ግን እያስከተለ ያለው ቀውስም ቀላል አይደለም፡፡ ከንቱ ወይም የማይጠቅሙ መረጃዎችን ለመቀበል የሚያስገድዱ ሁኔታዎችም ተፈጥረዋል፡፡ ለቤተክርስቲያን ቤተሰቦች ደግሞ መንፈሳዊ ሕይወትን ሊያውኩ የሚችሉ መረጃዎችም ይሠራጩባቸዋል፡፡ ከዚህ አልፎ ደግሞ ክብረ ነክ የሆኑ የሰዎችን ስምና ሥነ ልቦና የሚጎዱ መረጃዎችም ይሠራጩባቸዋል፡፡

ከእነዚህ ማኅበራዊ ሚዲያ አማራጮች መካከል ደግሞ ዩቱብ በተለየ ሁኔታ ትኩረት የሚስብ እየሆነ ነው፡፡ ዩቱብ በአንድ በኩል ለአዘጋጁ /መረጃውን ቀርጾ ከሚያሠራጨው አካል ከሚሰጠው የገንዘብ ጥቅም አንጻር እንዲሁም የመረጃ ተቀባዮች በምስልና ድምፅ ተቀናብረው ለሚሰጡ መረጃዎች እየሰጡ ካሉት ከፍ ያለ ግምት የተነሣ ትኩረት የሚስብ ሆኗል፡፡

ዩቱብ የሚዲያ አማራጭ ሆኖ ለቤተክርስቲያን አገልግሎት ካለው ዋጋ አንጻር የሚበረታታ ነው፡፡ በተለይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ካላት የድምጽ፣ የምስል፣ የክዋኔ ጥበብ ሀብት አንጻር ከፍተኛ ግብአት ስለሚኖራት አገልግሎትን በተከታታይነት በዚህ የሚዲያ አማራጭ እያሰፉ መሔድ የሚገባ ነው፡፡

በየጊዜውም በርካታ አገልጋዮች ዩቱብን አማራጭ ሚዲያ በማድረግ አገልግሎት እየሰጡ ነው፡፡ በዚህም በርካቶች እየታነጹ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ዩቱብ የምንወዳቸውን የምናምናቸውን አገልጋዮች ብቻ ሳይሆን የማናውቃቸውንም ተአማኒነት ተአማኒነት የሌላቸውንም ሰዎች በአገልጋይነትና በቤተ ክርስቲያን ተቆርቋሪነት እያስተናገደ ነው፡፡

በርካታ ዩቱዩበሮችም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን የአገልግሎት ፍሬዎች በመጠቀም፣ መለያ ትእምርቶቿንና ባህሏንም በመላበስ የተለያዩ መረጃዎች በመስጠት ላይ ናቸው፡፡ እነዚህን ዩቱብ ቻናሎችም በርካታ ምእመናን እየጎበኟቸው ስለሆነ የተመልካቻቸውን ቁጥር ማስፋትም እየቻሉ ነው፡፡

ዋናው ፈታኝ ነገር ግን እነዚህን በቤተክርስቲያን ስም አገልግሎት እየሰጡ ያሉ በታወቁም ባልታወቁም ግለሰቦች ስም ያሉ ዩቱብ ቻናሎችን የሚቆጣጠረው፣ የሚሰጡትንም

መረጃ ትክክለኛነት እያጣራ የሚያበረታታው ወይም የሚያርመው ወይም ወንጀል ነክ ሥራዎችም ሲሠራባቸው የሚጠይቀው ማነው የሚለው ነው፡፡ እነዚህ ዩቱብ ቻናሎች ቤተክርስቲያንን የሚጠቅሙ መስለው ጀምረው ቤተክርስቲያንን በሚጎዳ መንገድ ቢጨርሱ ለሚደመጣው ቀውስስ ተወቃሹ ማነው? በዚህ መንገድ ቢጾ ሐሳውያን አለመፈልፈላቸውን መከታተል የሚቻለው እንዴት ነው? ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹በውሸተኞች ወንድሞች በኩል ፍርሃት ነበረብኝ፤›› (፩ኛ ቆሮ.፲፩፥፳፮) እንዳለው ለቤተክርስቲያን የሚያስፈሩ አስመሳዮች ቢበዙባትስ የሚለውን ጥያቄ መመለስ ያስፈልጋል፡፡

የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች፣ ቤተሰቦች መስለው ቤተ ክርስቲያንን ጉዳት ሲያደርሱባት የታየው ገና ከመጀመሪያው ምእተ ዓመት ጀምሮ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ተመሳስሎ ቤተክርስቲያንን መጉዳትም የሰይጣን አንዱ አካሔድ ነው፡፡ ሐዋርያው ‹‹ነገር ግን ባሪያዎች ሊያደርጉን በክርስቶስ ኢየሱስ ያለንን አርነታችንን ይሰልሉ ዘንድ ሾልከው በስውር ስለ ገቡ ስለ ሐሰተኞች ወንድሞች ነበረ፡፡›› (ገላ.፪፥፬) ያለውን ማስታወስ ግድ ነው፡፡

እነዚህ ዩቱብ ቻናሎች ለአንድነት የሚሰብኩን መስለው ቤተ ክርስቲያንን የሚከፋፍል ሥራ ውስጥ ቢገቡ አቁሙ!›› የሚለው ማነው? እነዚህ ዩቱቦች ትክክለኛ ነገረ ሃይማኖት የሚሰብኩ መስለው በኋላ ኑፋቄን አስረገው ቢያስገቡና ቢከፋፍሉን በሕግ አምላክ የሚላቸው ማነው? እነዚህ ዩቱቦች ጽድቅን የሚሰብኩ መስለው ጀምረው ኃጢአትን ቢያስተዋውቁብን ለሚያመጣብን ስላቅ ዋጋ የሚከፍለው ማነው?

የዩቱቦችን መስፋፋት ለታዘበ ሰው እነዚህና መሰል ጥያቄዎች እንደ ምእመን ሊያሳስበው እንደሚችል እሙን ነው፡፡ ከማሳሰብም ባለፈ አልፎ አልፎ እየታዩ ያሉ አባቶችን ከአባቶች፣ ሰባክያንን ከሰባክያን የሚለያዩ ለሰላም ሳይሆን ለጠብ ለክርክር የሚሠሩ ታይተዋል፡፡

በተለይ አሁን፣ አሁን ቤተክርስቲያናችን በሀገራችን ያለውን የፖለቲካ ምስቅልቅ ተከትሎ እየደረሰባት ካለው ጫና አንጻር እነዚህ ዩቱቦች ለሜራ ጥቅም ላይ ላለመዋላቸው ዋስትናው ምንድነው?

ቤተ ክርስቲያን ከነገድ ከጎሳ ጋር አያይዞ፣ ከተለየ የፖለቲካ ቡድን ጋር አያይዞ እያራገቡ ለቆዩና ሊቆዩ ለሚችሉ አጥፊ አካሔዶች ማቀላጠፊያ ሊያገለግሉ አይችሉም ብሎ መናገር እንዴት ይቻላል፡፡ ‹‹አጥማቂና ባሕታውያን ነን›› የሚሉ ግለሰቦችስ እነዚህን ዩቱብ ሚዲያ አማራጮች እንዴት በአሉታዊ መንገድ እየተጠቀሙባቸው እንዳሉ በቀላሉ መታዘብም ይቻላል፡፡

በዩቱብ የሚገኘው ጥቅምም የቤተክርስቲያንን አገልግሎት ጉዳዮች ሁሉ ወደ መሸቀጥ እንዳይወስድም የሚያስፈራ ነው፡፡ አገልግሎትን ማስፋት እንዳለ ሆኖ፣ የሚበረታታም ሆኖ የሃይማኖት መልክ ይዘው በቀጥታ ለዩቱብ ንግድ ቤተክርስቲያን ላይ የሚሰለፉ ብዙ እንዳይሆኑ የሚያግድ ምን አስተዳደራዊ ሥርዓት አለ?

መንግሥትና ሌሎች ዓለማዊ ተቋማት የተቸገሩባቸውን የተዛቡ፣ ስም የሚያጠፉ፣ የተጋነኑ፣ የማያንጹ ወዘተ ተብለው ሊወስዱ የሚችሉ መረጃዎችን ከቤተ ክርስቲያን አንጻርም በመልቀቅ የምእመናንን አንድነት፣ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደርን ጥንካሬ የሚፈታተኑበት ዕድል እንደማይኖር ዋስትና መስጠት አይቻልም፡፡

ከምንም በላይ ደግሞ በቤተክርስቲያን ስም በተለመዱ ዩቱብ ቻናሎች በሚለቀቁ መረጃዎች የቤተክርስቲያን ቤተሰብ ከሌሎች እምነት ተከታዮች ጋር በሀገር ዜግነት በሚኖረው ትብብርና አንድነት ላይ ስጋት የሚያስከትል ነገር እንደማያሠራጩ ምን ዋስትና አለን? ይህ በዚህ ወቅት በተለይ እጅግ አሳሳቢ ነገር ነው፡፡

የበለጠ የሚያሳስበው ደግሞ መግታት ወይም መቀነስ ካልተቻለ ነው፡፡ ምክንያቱም የተወሰኑ ምእመናን ይህንን ከ‹‹ክርስቲያን አክቲቪዝም›› ጋር አያይዘው እንደ እቅበተ እምነት በመቁጠር እንዲበረታታ ሲፈልጉ ሌሎች ደግሞ ከላይ የጠቀስናቸውን ስጋቶች ታሳቢ ባደረገ መንገድ እንዴት ይገሩ የሚለው ያሳስባቸዋል፡፡

ስለዚህ ነገሩን እኛ እንደታዘብነው በውል ታዝቦ ከቤተ ክርስቲያን አስተዳዳር ጋር ተናቦ መራመድ ያስፈልጋል፡፡ የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳር በተቻለ መጠን በሆነ የታወቀ መመዘኛ ለቤተክርስቲያን ቤተሰቦችና ቤተ ክርስቲያን እንደ ተቋም የምትሠራውን ሁሉ ማወቅ ለሚገባቸው አካላት እውቅና ሰጥቷቸው አገልግሎት ላይ ያሉና እንዲኖሩ የሚፈለጉ ዩቱብ ቻናሎችን በየጊዜው ቢያሳውቅ ጥቅሙ ከፍተኛ ነው፡፡ በተቻለ መጠንም እነዚህን ሚዲያ አማራጮች ተከታትሎ ይዘታቸውን የሚያጠና /Media monitoring/ የይዘት ትንታኔ የሚሠራ አካል ሊያስፈልግ ይችላል፡፡ ይህም ችግሮች ከመስፋታቸውና የተዛቡ መረጃዎች በስርጭት ከመስፋፋታቸው በፊት ለጥፋት የሚዳርጉ ነገሮች ከመናፈሳቸው በፊት ለመቆጣጠር ለማረም እርምጃ ለመውሰድ ይጠቅማል ብለን እናስባለን፡፡

# ንቅሳቴን (ውቅራቴን) ባጠፋውስ?

ውድ የስምዐ ጽድቅ አዘጋጆች እንዴት አላችሁ? እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነኝ። ውስጤ ለሚመላለሰው ጥያቄ መልስ ትሠጡኝ ዘንድ ወደ እናንተ ልጽፍ ብዕሬን አነሣሁ። ነገሩ እንዲህ ነው ቤተሰቤና የተወልድኩበት አካባቢ በንቅሳት ማጌጥን የሚያድንቅ በመሆኑ እኔም በልጅነቴ አንገቴን ጨምሮ የፊቴን የተለያዩ ክፍሎች በንቅሳት ለማስጌጥ ተገድጄ ነበር። ይህ ሁኔታ በተወልድኩበት አከባቢ እያለሁ አብዛኛው ማኅበረሰብ ይጠቀምብት የነበረ ማጌጫ በመሆኑ በአሉታ አላየውም ነበር።

ነገር ግን በትምህርት ምክንያት ወደ ዩንቨርሲቲ ስገባ በተለየ አስተያየት የሚያዩን በዙ። ነገሩ የተናቀና አላስፈላጊ አድርጌ እንዳስበው አደረገኝ። ይህ ነገር ጭንቀት ፈጥሮብኝ ለብዙ ዓመታት አሳልፌያለሁ። ከትምህርት ዓለም ወጥቼ ሥራ ከያዝኩ በኋላ ነገሩን እንዴት ላጠፋው እንደምችል ማሰብና መጠየቅ ጀመርኩ። በአጋጣሚ ግን ቀላል በሆነ የሕክምና ጥበብ በውጪ ሀገር ሕክምና ሊጠፋ እንደሚችል ተነገረኝ። ዕድሉን አግኝቼ አሁን በውጪ ሀገር ለመኖር ለጉዞ እየተሰናዳሁ ነው። ታዲያ ይህንን አጋጣሚ ተጠቅሜ ንቅሳቱን ከሰውነቴ ላይ ባጠፋው ከክርስትና ሕይወቴ አንጻር የሚነቀፍ ነገር ይኖረው ይሆን። እስኪ ምከሩኝ።

ውድ ጠያቂያችን! ላነሡት ጥያቄ ከፍተኛ አክብሮት አለን። የእርስዎ ጥያቄ ምን አልባትም የበርካታ ከገጠሩ ማኅበረሰብ የወጡ ልጆች ጥያቄ ሊሆን እንደሚችል እናስባለን። ንቅሳት በኢትዮጵያውያን ዘንድ እንደ አንድ የማጌጫ ባህል ተይዞ የቆየ እንጂ በቤተክርስቲያን መምህራን ዘንድ ግን የተከለከለ እንጂ የሚበረታታ ሆኖ የቆየ አይደለም።

ቤተክርስቲያን እንኳን በሰውነት ላይ ቆስሎ ደምቶ የተሠራ ጌጥን፣ ከሰውነት ውጪ የሆኑ አጓጉል የማጌጥ አካሄዶችን የምትፈቅድ አይደለችም። በእርግጥ ማጌጥ በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ ለተለያዩ ምክንያቶች ይደረግ እንደነበር እናስተውላለን።

ነገር ግን ጌጥ የሚደረገው ነገርና የሚደረግበት ምክንያት የራሱ አካሄድ ነበረው። ሰዎች ከሰውነታቸው ውጪ በሆነ መንገድ ያማረ፣ የተወደደ፣ የተመረጠ፣ የተከበረ፣ የነጣ፣ ልብስ፣ጫማ ወይም በተለያዩ የአካል ክፍሎች ላይ ሊደረግ የሚችል ከተወደዱ ነገሮች/ማዕድናት ወይም ሌሎች ቁሶች/ ወስደው ሊጠቀሙ ይችላሉ። ይህንንም እጅግ በጣም በሕይወታቸው ልዩና የሕዝብ ሆነው በሚታዩባቸው አደባባዮች ሲገለጡ የሚያደርጓቸው ነበሩ።

የዚህ ሁሉ ዋነኛ ምክንያት በአደባባይ ሊውሉ የፈለጉበትን ዓላማ ለማድመቅ በማሰብ ነው። ዕንቊ፣ ብርና ወርቅ ለዚህ ያገለግሉ ነበር። ለምሳሌ አንድ ንጉሥ ወይም ሙሽሮች ለመክበር፣ ተለይቶም ደምቆ ለመታየት ጌጥን ሊያደርጉ ይችላሉ። በሌላም በኩል ሌላውን ለማክበር ጌጥ ሊደረግ ይችላል። አንድ ሰው ተከብሮ በተጠራበት ሠርግ ወይም ሌላ ድግስ ላይ ጌጠኛ ልብስ ወይም ጫማ ወዘተ አድርጎ ቢገኝ ራሱን ለማክበር ብቻ ሳይሆን ጠሪዎቹን አክብሮ መገኘቱም ይታሰባል። ይህ ሰውን ለማክበር ወይም በተለየ ሁኔታ ውስጥ ራስን ለማክበር የሚደረግ ጌጥ መጽሐፋዊ ምንጭ ስለ አለው አይደለም (ማቴ. ፳፪፥፲፩–፲፬ )።

ማጌጥ በዓላማውና በአፈጻጸሙ ሊነቀፍ ይችላል። አንድ ሰው የማመንዘር ዕቅድ ይዞ ለማጌጥ ቢነሣሣ ከመንፈሳዊ ሕይወት አንጻር የሚያስነቅፍ ይሆንበታል። በሌላ በኩል ራስን አክብሮ ካለመቀበል የራስን ተፈጥሮም ከማቃለል የመነጨ ሲሆን፣ ፈጣሪን እንደመቃወም ይሆናልና ያስነቅፋል። ከዚያም አልፎ አካልን አድምቶ አቁስሎ ወዘተ የሚደረግ ጌጥ ተነቃፊ ነው።

ውድ ጠያቂችን! እርስዎን ያጋጠመዎት ዓይነት ንቅሳትን በመሰለ አድሚና አቁሳይ አካሔድ ሊያጌጡ የሚሞክሩም አሉ። ከዚያም አልፈው የላስቲክ ቀዶ ጥገና በማድረግ አካላዊ ቅርጻቸውን እስከመለወጥ የሚራመዱም አሉ። እነዚህ ሁሉ ከሚነቀፉት አጊያጊጦች መካከል ናቸው። ክርስትናን በሚቃወሙ፣ ኃጢአትን በሚሰብኩ ማናቸውም ዓይነት ጌጦችም ለመዋብ መሞከር የማይገባ ነው። በእርግጥ ንቅሳት በጥንት አባቶቻችን ዘመንም አሁንም ድረስ በአንዳንድ ትጉሃን አበው እምነት የክርስቶስን ሞትና ትንሣኤ ለመመስከር፣ ለእምነታቸው ያላቸውን ቃል ኪዳን ለማጽናት ወዘተ በመስቀል ምልክት የሚወቀሩ አሉ። ይህ ዓላማውም ክርስትናን ማእከል ያደረገና ለሰማዕትነት ራስን ያዘጋጁበት አኗኗር በመሆኑ ከጌጥ አንጻር የሚታይ አይደለም። የክርስቲያናዊ ሕይወታቸው አንድ አካል ነው።

በሌላ በኩል ግን በተለያዩ ማኅበረሰቦች ዘንድ ንቅሳትን (ውቅራትን) ለተለያየ ዓላማ እንደሚያውሉት(እንደሚያስቡት) ግልጽ ነው። በአንዳንዶች ዘንድ ንቅሳትን ለእንቅርት ማጥፊያ እንደሚሆን በማሰብ ሌሎች ደግሞ ከመንፈስ በሽታዎች መዳኛ አድርገው በማሰብ ወዘተ ይወቀራሉ። ይሁን እንጂ ይሄ አካሔድ የበለጠ ለሰይጣናዊ ወጥመድ የሚጋብዝና አንዳንዶችም ለባዕድ አምልኮ ጭምር ሕይወታቸውን እንዲሰጡ ሲያደርግ ቆይቷል።

ውድ ጠያቂያችን እንዲገነዘቡት የተፈለገውም በእርስዎ ሕይወት ውስጥ የተፈጠረው ነገር አሁን ላይ ንቅሳቱን ለማጥፋት ካነሡት ጥያቄ ጋር ተያይዞ ሳይሆን አስቀድሞም ንቅሳቱ በሰውነት ላይ የባሕርይ እስኪመስል ማጣበቁ የተነቀፈ ነው።

ማጌጥ የባህል መሠረት ያለው ነገር ነው። ከመንፈሳዊው ሕይወት አንጻር የሚደርስበትን ነቀፌታ ብንገፋው እንኳን ባህል ተለዋዋጭና በሂደት ልዩ ልዩ መልክና ቅርጽ የሚይዝ ከመሆኑ የተነሣ በሰውነት ላይ ለምንግዜም ተጣብቀው እንዲኖሩ የምናደርጋቸው ማጌጫዎቻችን በትውልዶች መካከል ተቀባይነት የሚያሳጡ፣ የሚያስንቁ፣ ክብርና ተወዳጅነትን የሚቀንሱ ሆነው ሊገኙ ይችላሉ። ጠያቂያችንም ያጋጠመዎት ስሜት ከዚህ ተቀባይነት ማጣት የመነጨ ነው።

አሁን ያሉበት ሁኔታ በማኅበረሰባችን አባባል ‹‹መጀመሪያ ባልዘፈንሽ፣ ከዘፈንሽ ባላፈርሽ… ዓይነት ሆኗል። በእኛ በኩል

ጠያቂያችን እንዲጠነቀቁ የምንመክረው ከጉዳት ወደ ጉዳት በሚያመራ ሁኔታ ውስጥ እንዳያልፉ ነው፡፡ ንቅሳቱ ከጎዳዎት በላይ ንቅሳቱን ለማጥፋት የሚሄዱበት መንገድ እንዳይጎዳዎት እንሰጋለን፡፡

ንቅሳቱን ለማጥፋት ባሕር አቋርጦ ወንዝ ተሻግሮ መሄድ ምን አልባትም ያሉብትን ጭንቀት ያመለክታል፡፡ ይሁን እንጂ በራሱ ለዚህ ዓላማ ይህን ያህል ዋጋ መክፈል ለምን ብለው መጠየቅ አለብዎት እንላለን፡፡ ንቅሳቱን ማጥፋት ሕክምና የሚፈልግ ከሆነ ለሕይወትዎ አደጋ በሚያመጣ ሁኔታ ውስጥ ላለማለፍዎ ምን ዋስትና አለ፡፡ እንደዚህ ዓይነት ነገሮች የሚከናወኑት ቀላል በሚባሉ የቀዶ ጥገና ሕክምናዎች እንደሆነ ይሰማል፡፡ ቀላል ማለት ግን ምን ያህል የስሜት የገንዘብና የጊዜ ዋጋ እንደሚያስከፍል ለመገመት ይከብዳል፡፡

ሌላው ወሳኙ ነገር ግን ሰውነትን ያህል ክቡር ነገር ከልጅነት ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ መድማትና መቁሰል ተፈርዶበት ማየት በእጅጉ ሊያሳዝን ይችላል፡፡ ለእርስዎም ለውስጥዎ ሰላም የሚሰጥ አይሆንም፡፡ ንቅሳትን ለማጣበቅ የፈሰሰ ደም ነበር፡፡ ይሁን እንጂ እስካመኑበት ድረስ ጌጥ እንደሆነ አምነው ተቀብለውት ቆይተዋል፡፡ አሁን ደግሞ የትናንቱ ተግባር አላስፈላጊ መሆኑን በመንፈስም በሥጋም መንገድ መዝነውት ተገቢ አለመሆኑን ተገንዝበዋል፡፡

አሁን ደግሞ ንቅሳቱን ለማስወገድ የሚሄዱበትንስ መንገድና ዓላማ ከትናንት መንገድዎ በምን ይለያል፡፡ ንቅሳቱ አስቀድሞም ተፈልጎ የነበረው ‹‹ለመዋብ›› ነበር፡፡ አሁንም ቢሆን ንቅሳት ማጥፋቱ የተፈለገው ‹‹ለመዋብ›› ነው፡፡ በዓላማ ሁለቱም ደም አፍሳሽ መንገዶች አንድ ናቸው፡፡ ንቅሳቱን ለማጣበቅ የደረሰብዎ ሥቃይ አሁን ከሚደርስብዎ ቀዶ ጥገና ሕክምና የተለየ አይደለም፡፡

በመንፈሳዊ ሁኔታም ሲታይ ክቡር ሰውነትን ከማዋረድ አንጻር ትናንት ከሔዱበት መንገድ አሁኑ የተለየ አይደለም፡፡ ምን አልባትም አሁን ልብ አግኝተው ንቅሳቱን የነቀሉበት መንፈስ የበለጠ ሊያነቃዎትና ንቅሳት ለማጥፋት የሚገቡበትን ድካም ለማስወገድ ሊረዳዎት ይገባል፡፡ ይህ ካልሆነ ነገሩ ከቅምጥልነት የመነጨ ተደርጎ ሊታሰብብዎት ይችላል፡፡ ይህ ነገር መንፈሳዊ ሆነው ለመኖርም ፍላጎት ላለዎት ጠያቂያችን ተስማሚ ግብር አይደለም፡፡ ‹‹እንደ ሥጋ ፈቃድ ግን እንኖር ዘንድ ለሥጋ አይደለም›› (ሮሜ ፰÷፲፪) ካለው ከሐዋርያው ቃል አንጻር ሲታይ ለክርስቲያን አኗኗር የሚመከር አይሆንም፡፡

ከምንም በላይ ዋነኛው መመዘኛ ውቅራት ያስፈለገው ለምን ዓላማ ነው? የሚለውና የሥጋ ፈቃድን ጨቁነው ለነፍስ ፈቃድ ለሚገዙ ምእመናንን ውቅራትን መቀበልም ከዚያ ደግሞ ለማጥፋት መሯሯጥም ምን ያህል ከሕይወት መርህ ጋር ይስማማል የሚለው ነው፡፡

አስቀድሞም በውቅራት ብቻ ሳይሆን በቀለማት ተቀባብቶ መገኘትም በመጽሐፍ ቅዱሳችን ሳይቀር በዝሙት መተዳደር ለሚፈልጉ ሰዎች ተቀጽሎ የሚነገር ነበር፡፡ ለምሳሌ ‹‹አንቺም የተበዘበዝሽ ሆይ፥ ምን ታደርጊአለሽ? ቀይ በለበስሽ ጊዜ፥ በወርቅ አንባርም ባጌጥሽ ጊዜ፥ ዓይንሽንም በኵል በተኳልሽ ጊዜ፥ በከንቱ ታጌጫለሽ ውሽሞችሽ አቃለሉሽ፥ ነፍስሽን ይሹአታል፡፡›› (ኤር ፬÷፴) የሚለው የነቢዩ ቃል በምሥጢር ትርጉሙ ሌላ ይሁን እንጂ የተናገረበት ሰም ግን በማኅበረሰቡ ዘንድ የነበረውን አባባል መሠረት ያደረገ ነው፡፡

አንዲት ክርስቲያናዊት ሴት እንድትወደድ እንድትከበር እንድትፈቀር ሊያደርጋት የሚገባው ምንድነው ብለን ስናስብ ማጌጫዋ ምን እንደሆነ በዚያው ማስተዋል ይቻላል፡፡

ለምሳሌ ሐዋርያው ስለ ባለትዳሯ የአብርሃም ሚስት ሣራ ሲናገር ያለውን ቃል እናስተውል ‹‹ለእናንተም ጠጕርን በመሸረብና ወርቅን በማንጠልጠል ወይም ልብስን በመጎናጸፍ በውጭ የሆነ ሽልማት አይሁንላችሁ፥ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት ዋጋው እጅግ የከበረ የዋህና ዝግተኛ መንፈስ ያለውን የማይጠፋውን ልብስ ለብሶ የተሰወረ የልብ ሰው ይሁንላችሁ፡፡ እንዲህ በቀድሞ ዘመን በእግዚአብሔር ተስፋ ያደረጉት ቅዱሳት ሴቶች ደግሞ ለባሎቻቸው ሲገዙ ተሸልመው ነበርና፤…›› (፩ኛ ጴጥ ፫÷፫)

ይህ ለባለትዳሮች ብቻ ሳይሆን ክርስትናን በእምነት ከልብ ለመኖር ለሚሹ ሁሉ መጌጥ ያለባቸው በሌትና ቀን በክረምት በበጋ ሳሉ በጽናት ሊያጌጡበትና ሊዋቡበት በሚገባው በፍቅር፣ በትሕትና፣ በትዕግሥት፣ በበጎነት ወዘተ ነው፡፡ ይህ ሁሉ ጽኑና በዕድሜ ርዝማኔ፣ በአየር ንብረት ለውጥ፣ በባህል መፈራረቅ ምክንያት የማይዋዥቅና የማይናቅ ለሁሉም ማኅበረሰብ የሚጠቅም ጌጥ ነው፡፡ በዚህ መጌጥ የሥጋንም የነፍስንም ሕይወት ይጠቅማል፡፡

የክርስቶሳውን ውበት ብረት ከማንጠልጠል ሥጋን ከመከተል አይመነጭም፤ ትሕትና ገርንት የዋህነት ቸርነት ትዕግሥት በሥጋውያን ዘንድ እንደ ሞኝነት የሚታዩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ እንደ መጎዳት ይቆጥሯቸዋል፡፡ ነገር ግን አሸናፊና ተወዳጅ የሚያደርጉ የመንፈስ ጌጦች ናቸው፡፡ በሥጋችንም ላይ ያበራሉ፡፡ ጠቢቡ ‹‹እኔ ጥቁር ነኝ፤ ነገር ግን ውብ ነኝ›› (መኃ ፩÷፭) እንዳለው ያለ ነው፡፡

ውድ ጠያቂያችን በአጠቃላይ ስናየው ያነሡት ጥያቄ ንቅሳትን ለማጥፋት ያለዎትን ፍላጎት ምን አነቃቃው የሚለውን ውስጣዊ መሻትዎን በመገምገም የያዙትን አቋም ከክርስቲያናዊ የግብረ ገብ አስተምህሮ አንጻር ያጢኑት፡፡ ንቅሳት /ውቅራት የተቀበሉበትን ጊዜ ሲያስታውሱ በራስዎ ፈቃድና ተነሳሽነት አድርገውት ከሆነ በልጅነት መንፈስም ይሁን በሌላ ያደረጉት ነገር ከክርስቲያናዊ አኗኗር አንጻር የሚበረታታ አለመሆኑን ይረዱ፡፡ አሁን ደግሞ ያኔ ወደውት የነበረውን ነገር የአሁኑ ማኅበረሰብ ሲያናንቀው ደግሞ ዳግም በሰውነት ላይ መጫወት ዳግም ራስን መበደል ይሆንብዎታል፡፡ በተቻለ መጠን ብርቱ ክርስቲያናዊ መንፈስ በመላበስ በጸሎትም በመታገዝ ሌሎች በሕይወትዎ ሊጠቅሙዎት በሚችሉ ነገሮች ላይ ጊዜዎትን ገንዘብዎትን ያውሉ፡፡ ስሜትዎትንም እንዲሁ፡፡ ‹‹በሚሞት ሥጋችሁ ኃጢአት አይንገሥ (ሮሜ ፮÷፲፪) የሚለውን የሐዋርያውን ቃል በማስተዋል ይበረታቱ እንላለን፡፡

***ወስብሐት ለእግዚአብሔር!***